# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 114 ታኅሣሥ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# “ኢትዮጵያ

## ከሶማሊላንድ ጋር ያደረገችው ስምምነት ዝርዝር ሂደቱ ተጠናቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባር ይገባል”

- አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የተፈራረመችው ስምምነት ዝርዝር ሂደቱ ተጠናቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባር እንደሚገባ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለፁ፡፡

በስምምነቱ ዙሪያ ለጋዜጠኞች ማብራሪያ የሰጡት አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፤ ኢትዮጵያ ከሁሉም የጎረቤት አገራት ጋር በሰጥቶ መቀበል መርህ እየሠራች ትገኛለች ብለዋል።

ኢትዮጵያ እያደገ ያለውን ኢኮኖሚዋን ለመሸከም እና ብሄራዊ ጥቅሞቿን ማስጠበቅ እንድትችል የባህር በር እና የወደብ አማራጮች እንደሚያስፈልጋት የገለፁት አምባሳደሩ፤ ይህንንም በሰላማዊ መንገድ ብቻ ለማሳካት ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት ጥረት እያደረገች መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መሰረትም ከጎረቤት ሀገራት ጋር መተባበር እና ለጎረቤት ሀገሮች ቀድሚያ የመስጠት መርሆችን በመከተል ከሃገራቱ ጋር በሰጥቶ መቀበልና በምክክር ለመጓዝ መቻሉንም ተናግረዋል፡፡

ይህን ታሳቢ በማድረግ ከሶማሊላንድ ጋር የተለያዩ የዲፕሎማሲ ስራዎች ማከናወን መቻሉን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ በሁለቱ ሀገራት ከተደረሰው ስምምነቱ በፊት በመሪዎች ደረጃ ሰፊ ምክክር ሲደረግ መቆየቱንም ገልጸዋል፡፡

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የተፈራረመችው ስምምነት በማህበራዊ፣ በባህል፣ በጤና፣

“ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ4 ዞሯል






## የጤና መድህንን የጤና ሥርዓትን ሀገራዊ አቅም በሚያሳድግ መልኩ መተግበር ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የጤና መድህንን የጤና ሥርዓትን ሀገራዊ አቅም በሚያሳድግ መልኩ መተግበር እንደሚያስፈልግ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ብሔራዊ ምክር ቤት ጉባኤ ላይ

የጤና መድህንን ... ወደ ገጽ4 ዞሯል



ፎቶ፡ሀዱሽ አብርሃ

## የከሠም ስኳር ፋብሪካን በሙሉ አቅሙ ወደሥራ ለማስገባት አምስት ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አፋር፡- የከሠም ስኳር ፋብሪካን በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ለማስገባት አምስት ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተጠቆመ።

በፋብሪካው የኦፕሬሽን ዘርፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ ፈጠነ ዳባ እንደተናገሩት በአሁኑ ወቅት ፋብሪካው እያመረተ ያለው ከአጠቃለይ አቅሙ ከ23 በመቶ

የከሠም ... ወደ ገጽ4 ዞሯል

## ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ተፈጥሯዊ ፣ ታሪካዊና ሕጋዊ መብት እንዳላት ምሁራን ተናገሩ

**እስማኤል አረቦ**


ሀዋሳ፡- ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ ችግሮች ምክንያት ያጣችውን የባህር በር የማግኘትና የመጠቀም ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ሕጋዊ መብት እንዳላት ምሁራን ተናገሩ፡፡

“የአፍሪካ ቀንድ ጂኦፖለቲክስና የኢትዮጵያ የባህር በር አማራጮች” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ በወደብና በባህር በር ምንነትና አጠቃቀም ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበዋል፡፡

በዚሁ ውይይት ላይ የተገኙት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አያኖ በራሶ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በባህር የተከበበችና አፈጣጠሯም ከውሃ አካላት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡

በውስጥ በነበረ ቅራኔና በውጭ ጠላቶች አማካኝነት ወደብ አልባ እስከሆነችበትና የባህር በር ባለቤትነቷን

ኢትዮጵያ የባህር... ወደ ገጽ4 ዞሯል












የአብስራ ዘላለም

# ተቋሙ ለፓርኪንሰን ሕሙማን ድጋፍ የ500 ሺህ ዩሮ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ፓርኪንሰን ኢትዮጵያ የፓርኪንሰን ሕሙማንንና አስታማሚዎችን ህይወት ያሻሽላል የተባለለትና ቆይታውን ሶስት ዓመታት የሚያደርግ የ500 ሺህ ዩሮ ፕሮጀክት ትናንት ይፋ አደረገ፡፡

በተቋሙ የፕሮጀክት አስተባባሪዋ የአብስራ ዘላለም እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ ለሶስት ዓመታት ቆይታውን የሚያደርግና በተቋሙ በአባልነት ያሉ አንድ ሺህ 127 ታማሚዎችንና አስታማሚዎችን ለማደገፍም ይውላል፡፡ አስተባባሪዋ ፕሮጀክቱ ብሪድ ፎር ዘ ወርልድ ከተሰኘ የጀርመን ግብረሰናይ ድርጅት በተገኘ አምስት መቶ ሺህ ዩሮ ድጋፍ እንደሚከወን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አስተባባሪዋ ንግግር፤ ፕሮጀክቱ ወደ ከአራት ክልሎች ማለትም ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ኦሮሚያ፣ ትግራይና አማራ ክልሎች ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዷል፡፡

ፕሮጀክቱ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ከጤና ሚንስቴር፣ ጤና ቢሮዎችና የመድሀኒት አስመጪዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላትን የማማከር ስራዎችን ሰርቷል ሲሉም አስተባባሪዋ አስረድተዋል፡፡

ተቋሙ ለፓርኪንሰን ታማሚዎች የፊዚዎቴራፒ፣ ስፒች ቴራፒ ከከነማ ጋር በመነጋገር የመድሀኒት አቅርቦት እንዲኖር የማድረግና የስልጠና አገልግሎቶችን ይሰጣል ሲሉ አስተባባሪዋ ተናግረዋል፡፡

በጤና ሚንስቴር ተላላፊ ህመሞች ተወካይ የሆኑት ዶክተር ሰላማዊት አያሌው በበኩላቸው፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ተጋላጭነት ስለመጨመሩ ጠቅሰው በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት ብቻ 3 ሺህ 647 የፓርኪንሰን ህሙማን በጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደ ተወካይዋ ንግግር፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአዕምሮ ጤና ነርቭ እና ለሱስ ችግር ህመሞች ካለፉት ዓመታት በተሻለ መልኩ ትኩረት የተሰጠበት በሀገሪቷ ጤና ስትራቴጅ የማህበረሰብ የጤና ጉዳይ በመሆኑ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ይህንንም ስትራቴጂ ለመፈፀም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማካተት እና በተቀናጀ መልኩ ለችግሩ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ለመላዉ ማህበረሰብ ክፍል ለማዳረስ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ፓርኪንሰን ህመም በአብዛኛው ከእድሜ ጋር ተያይዞ በሚከሰት የአንጎል ህዋሳት መመናመን የሚመጣ የመንቀሳቀስ ችግር ነው። የአንጎል ህዋሳት ተራ በተራ ሲሞቱ በነዚህ ህዋሳት የሚከወን ስራ በመስተጓጎሉ የሚፈጠር አስቸጋሪ ህመም ነው።

ፓርኪንሰን የተባለው የህክምና ባለሙያ ስለዚህ ችግር ላደረገው ምርምርና የተጠናከረ አቀራረብ በስሙ ህመሙ ተሰይሞለታል።

# “ገናን በላሊበላ ጥምቀትን በጎንደር ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል”

\- አቶ ጣሂር ሙሐመድ
የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡-ገናን በላሊበላ ጥምቀትን በጎንደር ለማክበር የሚሄዱ እንግዶችን ለመቀበል ከማህበረሰቡ ጋር እየተሰራ መሆኑን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ጣሂር ሙሐመድ አስታወቁ።

የትራንስፖርት ችግር እንዳያጋጥም ተጨማሪ በረራዎች እንደሚደረጉ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር ውይይት መደረጉንም ጠቁመዋል።

አቶ ጣሂር ሙሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ገናን በላሊበላ ጥምቀትን በጎንደር ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ከማህበረሰቡ ጋር እየተሰራ ነው፡፡

በክልሉ ከታህሳስ መጨረሻ ቀናት ጀምሮ የሚከበሩ በርካታ ባህላዊና ሐይማኖታዊ ክብረ በዓላት አሉ ያሉት አቶ ጣሂር፤ በዓላቱን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

ለክብረ በዓላቱ በየአካባቢው ካለው ማህበረሰብ፣ ከመንግስት አካላትና ከሐይማኖት አባቶች የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ መገባቱን አስታውቀው፤ በዓላቱ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበሩ እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል።

ለክብረ በዓላቱ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል



አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መዘጋጀታቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ በተለይም ለአካባቢው ማህበረሰብ ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ የሚያስገኝ በመሆኑ እንግዶቹን ለመቀበል መዘጋጀቱን ተናግረዋል፡፡

ክብረ በዓላቱ ምዕመኑ ከሚያገኛቸው መንፈሳዊ ፋይዳዎች ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዳላቸው ጠቁመው፤ ለክብረ በዓላቱ የትራንስፖርት ችግር እንዳያጋጥም ከአየር መንገድ ጋር በመነጋገር ተጨማሪ የአየር በረራዎች እንደሚደረጉ መገለጹን አስረድተዋል።

የቴሌኮም ኔትወርክ መቆራረጥ እንዳያጋጥም፣ ሆቴሎችና የተለያዩ ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉና በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የቱሪዝም ዘርፍ ለበርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው በመሆኑ፤ ለክብረ በዓላቱ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ ዝግጅት እያደረጉ መሆናቸውንና የተጋነነ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳያጋጥሙ በጥንቃቄ እየተሰራ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

በሰላም እጦት ሳቢያና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ባለፉት ዓመታት የቱሪዝም እንቅስቃሴው ከፉኛ ተጎድቶ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በጸጥታ ሃይሉ በተሰሩ በርካታ ሥራዎች አማካኝነት የክልሉ የጸጥታ ሁኔታ መሻሻል እንደታየበት ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም ዘርፉን ወደ ነበረበት ለመመለስ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማነቃቃት የማርኬቲንግና የማስታወቂያ ስራዎች በስፋት እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በሀገር ውስጥና በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ ጎብኚዎች መጥተው አካባቢውን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ከ60 በላይ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ማህበራት ለመንግሥት ምስጋና አቀረቡ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ከ60 በላይ የታክሲ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት አገልግሎት ሲሰጡባቸው የነበሩበትን አሮጌ ታክሲዎች በተለምዶ "ላዳ ታክሲዎች" ወደ ዘመናዊ የታክሲ መኪኖች እንዲቀይሩ መንግሥት ከቀረጥ ነጻ በመፍቀድ ላደረገው አስተዋጽኦ ምስጋና አቀረቡ፡፡ ማህበራቱ ለስምንት መንግሥታዊ ተቋማትም እውቅና እና ምስጋና ሰጥተዋል፡፡

የማህበራቱ ተወካይ አቶ ብርሃኑ ገብረመድህን በመድረኩ ባደረጉት ንግግር ላለፉት ዓመታት ህብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት እንዳያገኝ አብዛኛዎቹ ተሽከርካሪዎች ለረዥም ጊዜ አገልግሎት በመስጠታቸው በየቦታው በብልሽት የሚቆሙ እና በተጠቃሚዎች ዘንድ ተመራጭ እንዳልነበሩ አስታውሰው መንግሥት በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በዘርፉ ያሉትን ችግሮች በመረዳት ለማህበራት ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሆኑ ተሽከርካሪዎች እንዲፈቀዱ እንዲሁም ችግሩ ዘመናዊና ዘላቂ መፍትሄ እንዲኖረው አቅጣጫ በመስጠት የላቀ ሚና ማበርከታቸውን ተናግረዋል፡፡

የማህበራቱ ተወካይ እንደገለጹት፤ ገንዘብ ሚኒስቴር ፣የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ይህ ፕሮጀክት ዕውን እንዲሆን ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል፡፡

ከ60 በላይ የሚሆኑት ማህበራት እያንዳንዳቸው ከ40 እስከ 50 አባላትን ያቀፉ እና በአጠቃላይ ወደ ሶስት ሺህ የሚጠጉ አባላት ያሏቸው መሆናቸውን ተናግረው፤ ማህበራቱ ሲቋቋሙ ዘመናዊ፣ ምቹ፣ቀልጣፋ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ዓላማ አድርገው መነሳታቸውን ጠቁመዋል፡፡

ማህበራቱ ባለፉት ዓመታት በአዲስ አበባ በአሮጌ ተሽከርካሪ የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ የቆዩ እንዲሁም ከተለያዩ የሙያ መስኮች ወደ ትራንስፖርት ዘርፍ ለመሰማራት በማለም የተደራጁ መሆናቸውንም ገልጸዋል፡፡

የትራንስፖርት አገልግሎቱ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ



እንዲሰጥ መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር በጋራ መስራቱን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የተናገሩት አቶ ብርሃኑ፤ ማህበራቱ ከአክሎክ ሞተርስ ጋር ባላቸው ውል መሰረት እየተረከቡ ያሉትን ዘመናዊ መኪኖች ሰሌዳ እንዲያገኙ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግም በመድረኩ ጠይቀዋል።

እንደ አቶ ብርሃኑ ገለጻ፤ የትራንስፖርት ማህበራቱ በቀጣይ በዘርፉ ያላቸውን ልምድ ተጠቅመው በአዲስ አበባ በሚገኙ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች፣ሆቴሎች፣ኤርፖርቶች፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ለከተማዋ የኢኮኖሚ መነቃቃት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለመወጣት ዝግጁ ናቸው፡፡

በምስጋና መርሀ ግብሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት፣ገንዘብ ሚኒስቴር፣፣የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን እና ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የምስጋና የምስክር ወረቀት ከእለቱ የክብር እንግዳ ከአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር ተቀብለዋል፡፡

ማህበራቱ ከመንግሥት በተጨማሪ በፋይናንስ የደገፋቸውን አሚጎስ የቁጠባና የብድር ተቋም እንዲሁም መኪኖቹን በመገጣጠም የሚያቀርበውን አክሎክ ሞተርስን አመስግነዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር ፣የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳዉ (ዶ/ር)፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የማህበሩ አባላት ተገኝተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስኬት የታየበት ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስኬት የታየበት መሆኑን የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሥራ አስፈጻሚ በሪሶ አመሎ (ዶ/ር) ከሱማሌ ላንድ ጋር የተፈረመውን የባህር በር የመግባቢያ ስምምነትን ተከትሎ ትናንት በሰጡት መግለጫ ፤ ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ስኬት የታየበት ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት በኢኮኖሚ፣ በዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ጫና ነበረባት ያሉት ዶክተር በሪሶ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ከሱማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ጋር ያደረጉት የመግባቢያ ስምምነት ለዘመናት ኢትዮጵያ ላይ የተቆለፈውን በር የሚከፍት ነው ብለዋል፡፡

የባህር በር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሳድግ፣ ተሰሚነትን የሚጨምር፣ ሉዓላዊነትን የሚያሳድግ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ከሀገራት ለመገናኘት፣ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት፣ ለመነገድና እቃዎችን ለማጓጓዝ የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል።

የእራሳችን የሆነ የባህር በር መከፈት ለኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ እንደ ተቋም ከፍተኛ እድልን የሚፈጥር መሆኑን የጠቆሙት ሥራ አስፈጻሚው፤ መርከቦች በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ለማስቻልና ምርቶችን ለውጪ ገበያ ለማቅረብ ከውጪም ምርቶችን ለማስገባት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

የባህር በር አለመኖር ምርቶችን በሚፈለገው ጊዜ ለማጓጓዝ ከፍተኛ ጫና እንደነበር በመግለጽ፤ በተለይም የወደብ ባለቤቶች አስገዳጅ ህጎችና የዋጋ ጭማሪዎች በሀገሪቱ ገቢና ኢኮኖሚ ላይ ጫና ሲያስከትል ቆይቷል ሲሉ አመላክተዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱ ቀደም ሲል በወደቦች ላይ የነበረውን ጫና የሚቀርፍና የትራንስፖር ዋጋን የሚያሻሽል ነው ያሉት ዶክተር በሪሶ፤ በተለይም በዜጎች ላይ ይደርስ የነበረውን የዋጋ ጭማሪ እንዲሻሻል የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የባህር በር ለአንድ ሀገር ለንግድ እንቅስቃሴ፤ የሀገሪቱን



ዶክተር በሪሶ አመሉ

ግዛትና ሉዓላዊነት ለመጠበቅ የሚረዳ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ለዜጎች የሥራ እድልን በመፍጠር ሀገራዊ ኢኮኖሚንና ገቢን የሚያሳድግ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ጠንካራ መከላከያ ሰራዊትና አንድነቱ የጠናከረ ህዝብ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያ በባህር በር በነጻነት ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያስችላት ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

እንደሀገር የባህር በሩን ለመጠቀም የሎጀስቲክስ አቅም ለማሳደግ፣ አገልግሎትን ለማሻሻል፣ የዘመነና የሰለጠነ ተቋማዊ አሰራርን ለመዘርጋት መዘጋጀታቸውን በመግለጽ፤ ስምምነቱን መሰረት በማድረግ ትልቅ ዘመናዊ የሎጀስቲክስ ተቋም የሚገነባ ይሆናል ብለዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱ የመርከቦችን ብዛት ለመጨመርና የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት የሚያስችል መሆኑን የተናገሩት ዶክተር በሪሶ፤ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ሰፊ እድል ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበትን የመግባቢያ ስምምነት ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከሶማሌላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ ጋር ከትናንት በስቲያ መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡

# ዳያስፖራው ለሀገራዊ ጥሪው አበረታች ምላሽ እየሰጠ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በውጭ ሀገር ለሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያቀረቡትን ጥሪ ተከትሎ ከዳያስፖራው እየተሰጠ ያለው ምላሽ መልካምና አበረታች መሆኑን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ገለጸ፡፡

በአገልግሎቱ የዳያስፖራ ማህበረሰብ ልማት ዳይሬክቶሬት ተጠባባቂ ዳይሬክተር ነብዩ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በውጭ የሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ በሚኖራቸው ቆይታ ስለሀገራቸው ባህልና ታሪክ እውቀት እንዲኖራቸው ለማስቻል ታቅዶ በተጀመረው ንቅናቄ ከዳያስፖራው ወገን አበረታች ምላሽ እየተገኘ ነው፡፡

በውጭ የሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ ጥሪ የሀገር ፍቅር ስሜትን በመኮርኮር ሀገራቸውን በታሪክና በባህል እንዲቆራኙ እድል የሚሰጥ መሆኑን ያመላከቱት አቶ ነብዩ፤ በውጭ ሀገራት ያካበቷቸውን ልምዶች ሀገር ቤት ላሉ ወዳጆቻቸው እንዲያካፍሉ እድል ይሰጣል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ነብዩ ንግግር፤ ጥሪው ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ አባቶቻቸው የሰሩበትንና የገነቡትን ሀገር እንዲያስቀጥሉ ለማድረግ የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ በዳያስፖራው በኩልም ጥሩ የሆነ ንቅናቄ ስለመኖሩ እንዲሁም ፍላጎትና ጥያቄዎች መኖራቸውንም ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው ሀገራዊ ጥሪ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት ተፈጥሮ እንደነበር ያወሱት አቶ



ነብዩ ሰለሞን

ነብዩ፤ በአሁኑም ጥሪ በርካታ ቁምነገሮችን ለመስራት ስለመታቀዱ ተናግረዋል፡፡

ጥሪው በመሰረታዊነት ያላቸውን የእረፍት ጊዜ መሰረት ያደርጋል ያሉት አቶ ነብዩ በሶስት ደረጃዎች የሚደረግ ስለመሆኑ በመጥቀስ የአዲስ ዓመት እረፍትን፤ የፀደይ ወቅታቸውንና የእኛን ክረምት ተከትሎ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አቶ ነብዩ በንግግራቸው፤ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ያሉት የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ቀድመው መከረሚያቸውን ያቀዱ ቢሆንም የሌሎቹ እቅድ ከጥሪው ጋር የመገጣጠም ሁኔታዎች ስለመታየታቸው አመላክተዋል፡፡

የአሁኑ ጥሪም በታህና ጥር ወራት ያሉትን የአደባባይ በዓላትን በማክበር የባህል ትስስር የመፍጠሪያ እድል ሲሰጥ፤ የታሪክ ትስስርን በሚመለከትም የአድዋ በዓልን ተከትሎ ከፓንአፍሪካኒዝም የማስረፅ ስራዎች ይኖራሉ፡ ፡ የክረምቱ ጥሪም ለሁለተኛ ትውልደ ኢዮጵያውያኑ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ስለመሆኑ ጠቁመዋል፡፡

በቱሪዝም ሚኒስቴር የሚመራውና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በምክትልነት የያዘው ኮሚቴም አበረታች ተግባራት ስለመፈፀሙ አቶ ነብዩ ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ከክልልና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ትስስር በመፍጠር ኢትዮጵያውያኑ በሀገራቸው የሚገጥሟቸውን የቢሮክራሲና ሌሎችም ችግሮች የማቃለል ስራዎች በመስራት ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡



# የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ለገና በዓል አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አጠናቋል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ለገና በዓል አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ስራ ማጠናቀቁን የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት በትናንትናው እለት ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ አስታውቋል፡፡

የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰይድ እንድሪስ ጋዜጣዊ መግለጫውን በሰጡበት ወቅት እንደገለፁት፣ ድርጅቱ የ2016 ዓ.ም የገና በዓልን አስመልክቶ ጥራትና ፍጥነት ያለው አገልግሎት መስጠት የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት አድርጓል፡፡

ለበዓሉ 3000 በሬዎችና 5000 በግና ፍየሎች ለዕርድ ዝግጁ መሆናውን የጠቀሱት አቶ ሰይድ፤ ለስራው ፍጥነትና ጥራት ሲባል 250 ሠራተኞች በጊዜያዊነትና በተጨማሪነት ተቀጥረዋል ብለዋል፡፡ 35 የማሰራጫ መኪኖች፣ በቂ የእንሰሳት ማቆያ ጊዜያዊ በረቶች፣ የእርድ መሳሪያዎችና ሌሎችም አስፈላጊ ግብዓቶች ዝግጁ መሆናውንም ጠቁመዋል፡፡

በቁም እንስሳት አቅርቦትና በዋጋ ረገድ ችግሮች እንደሌሉና በቂ እንስሳትም እየገቡ መሆናቸውን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፣ ድርጅቱ ከሚሰጠው የእርድ አገልግሎት በተጨማሪ የበዓሉ እለት በድርጅቱ ዙሪያ በሚገኙ የመሸጫ ሱቆች የበሬ ስጋ በኪሎ ግራም ከ550 እስከ 570 ብር፣ የበግ ስጋ በ500 ብር የፍየል ስጋ ደግሞ በ510 ብር ለመሸጥ ዋጋ ተቆርጧል ብለዋል፡፡

ድርጅቱ በማታው ክፍለ ጊዜ ለልኳንዳ ቤቶች፣ ለሆቴሎችና ሬስቶራንቶች፣ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ደግሞ ለግል ተጠቃሚዎች አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ያስታወቁት ሥራ አስኪያጁ፣ ህብረተሰቡ የእርድ አገልግሎትን በቄራዎች ድርጅት እንዲያገኝ የተመቻቸ በመሆኑ በአገልግሎቱ እንዲጠቀምና ህገ ወጥ እርድን እንዲከላከል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ በቅርቡ ከእንስሳት እርድ ጋር በተያያዘ የተነዛውን ወሬ አስመልክተው ህገ ወጥ የበሬ፣ በግና ፍየል እርድ ቢኖርም፣ ከዚህ ውጪ ከባህላችንም ከእምነታችንም ውጪ የሆኑ የቁም እንስሳት ታርደው ወደ ገበያ የቀረቡበት ሁኔታ የለም ብለዋል፡፡ ወሬው ሐሰተኛ መሆኑንና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ መረጃ አሰራጭተዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦች ማጣራት እየተደረገባቸው መሆኑን አስታወቀዋል፡፡

በድርጅቱ ተገኝተው መግለጫ የሰጡት የአዲስ አበባ ልኳንዳ ቤቶች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ አቶ አየለ ሳህሌ በበኩላቸው፣ የተናፈሰው ወሬ እውነትነት የሌለው አሉባልታ ነው ያሉ ሲሆን፣ አሉባልታው የልኳንዳ ቤቶችን ገበያ በከፍተኛ ደረጃ እንዳቀዛቀዘውም ተናግረዋል፡፡

ማኅበሩ ልኳንዳ ቤቶችን በአባልነት ሲያቅፍ የአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ደንበኛ መሆናቸውንና ከንግድ ፈቃድና ግብር ጋር በተያያዘ ህጋዊነታቸውን አረጋግጦ መሆኑን የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ፣ የኢትዮጵያ ባህልና ወግ ከሚፈቅደው ውጪ የሆነ ተግባር እየተፈጸመ እንዳለ አድርገው ወሬ ያናፈሱ የአንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ሥራ አስኪያጅና አንድ ሰራተኛ በህግ ጥላ ስር ሆነው ምርመራ እየደረገባቸው እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ህብረተሰቡ ልክ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በሙሉ እምነትና ነጻነት የልኳንዳ ቤት አገልግሎትን እንዲጠቀምና በዓሉን በኢትዮጵያዊ ባህልና ወግ እንዲያከብርም ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

# ማህበሩ ጡረተኞች ያካበቱትን ልምድ ይዘው የተሻለ መሥራት እንደሚችሉ በተግባር አሳይቷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ማህበሩ ጡረተኞች ያካበቱትን ልምድ ይዘው የተሻለ መስራት እንደሚችሉ በተግባር አሳይቷል ሲሉ ፈለገ ኢቢሲ ንግድ አክሲዮን ማህበር የቦርድ ፕሬዚዳንት አቶ ዘሩ በላይ ገለጹ፡፡

የንግድ አክሲዮን ማህበሩ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ትናንትና ሲያካሂድ የአክሲዮን ማህበሩ የቦርድ ፕሬዚዳንት አቶ ዘሩ በላይ እንደገለጹት፤ ማህበሩ ጡረተኞች ያካበቱትን ልምድ ይዘው በተለያዩ ዘርፎች የተሻለ መስራት እንደሚችሉ በተግባር አሳይቷል።

ማህበሩ በካፌ ፣ በጽዳት፣ በጥበቃ ፣ በፐብሊክ ትራንስፖርት ዘርፍና እና በሌሎች የሥራ ዘርፎች እየሰራ ሲሆን፤ ለ246 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን አስረድተዋል፡፡

የንግድ አክሲዮን ማህበሩ አስፈላጊ የፈቃድ ሂደቶችን አጠናቆ ባለፈው በጀት ዓመት ጥቅምት ወር ላይ ወደ ሥራ ገብቷል፤ በዚህም በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት ከተገኘው ገቢ የግብዓት ግዢ፣ የሰራተኛ ደመወዝና የግብር ክፍያ ወጪ ተደርጎ አጠቃላይ የተጣራ ትርፉ ከ603 ሺህ ብር በላይ ነው ብለዋል፡፡

ማህበሩ በተቋቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያሳየው እንቅስቃሴ ጤናማ መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ፤ በዘንድሮው በጀት ዓመት ከ35 ሚሊዮን ብር በላይ ለማንቀሳቀስ ዕቅድ ተይዟል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በቅርቡ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በመስራት የሬዲዮ አየር ሰዓት ወስዶ አረጋዊያን ላይ የሚያጠነጥን ዝግጅት እያቀረበ ይገኛል ብለዋል፡፡

አቶ ዘሩ እንደገለጹት፤ አክሲዮን ማህበሩ የተቋቋመው በኢቢሲ በጋዜጠኝነት እና በሌሎች ቴክኒክ ሥራዎች ላይ ተቀጥረው ሲሰሩ የቆዩ እና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ ከ200 በላይ ባለአክሲዮኖች የመሰረቱት ነው፡፡

በስራ ዓለምም ሆነ በጡረታ ላይ የሀገርን ኢኮኖሚ መደገፍ ይቻላል ያሉት አቶ ዘሩ፤ ከድርጅቱ በጡረታ በሚወጡበት ጊዜ በሰራተኞች ላይ ስጋት ቢፈጠርም፤ የአክሲዮኑ መመስረት ሰራተኛው የሚደግፈኝ ድርጅት አለ ብሎ እንዲያስብ አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አክሲዮኑ በመመስረቱ ጠረተኞች ወደስራ ተመልሰዋል፤ አሁን ላይ ማህበሩ በስድስት የስራ ዘርፎች ተሰማርቶ እየሰራ ይገኛልብለዋል፡፡

የማህበሩ ካፒታል አናሳ መሆን የተወዳዳሪነት አቅማቸውን ዝቅተኛ ማድረጉንና ሰራተኛው ለበርካታ ዓመታት በሚዲያ ስራ ላይ ብቻ የቆየ በመሆኑ በንግድ ዘርፍ ላይ በቂ ዕውቀት ያለመኖሩ እንደተግዳሮት አንስተዋል፡፡

ያለውን የዕውቀት ክፍተት ለመሙላት ከአማካሪ ድርጅቶች ጋር ለመስራት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሌሎች ድርጅቶች ከኢበሲ ልምድ በመውሰድ ሰራተኞች ጡረታ ሲወጡ ተደራጅተው እንዲሰሩ በማድርግ ቢደግፏቸው ከቤተሰብ አልፈው የሀገር ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚኖራቸውን ሚና ማጎላት ይቻላል ሲሉ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

## “ኢትዮጵያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በትምህርትና መሰል ዘርፎች ላይ በትብብር ለመስራት የሚስችል እና በተለያዩ ዘርፎች በቀጣይ ለሚኖረው ግንኙነት እንደማዕቀፍ የሚያገለግል መሆኑን ተናግረዋል።

የመግባቢያ ሰነዱ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት ፍላጎት እውን የሚያደርግ፣ የባህር በር አማራጮችን የሚያሰፋ፣ የሁለቱን ወገኖች የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ፣ የፀጥታ እና የኢኮኖሚ ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋገር መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በስምምነቱ መሰረት ኢትዮጵያ በሶማሊላንድ የባህር በር እና የጦር ሰፈር እንዲኖራት እና በሂደትም የመሰረተ-ልማት ግንባታዎችን እንድታከናውን የሚያስችላት መሆኑን አምባሳደር ሬድዋን አስታውቀዋል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያ የበርበራ ኮሪደርን በስፋት ለመጠቀም እንዲያስችላት የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ላይ ተመስርቶ የባቡር እና የመንገድ መሰረተ ልማቶችን ለመዘርጋት አድል የሚፈጠር መሆኑንም ነው የገለፁት፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ የኢትዮጵያ መንግስት በሰጥቶ መቀበል መርህ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የመስራት ፍላጎቱን እና አቋሙን የሚያፀና መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ በስምምነቱ ሶማሌላንድ በንግድ እና በአቅም ግንባታ ዘርፍ ከኢትዮጵያ ጋር በጋራ ለመስራት እንደሚያስችላትም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር በተፈራረመችው የስምምነት ማዕቀፉ ውስጥ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚገኙበትም አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገልፀዋል።

## ኢትዮጵያ የባህር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እስካጣችበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ ፲ሺ 800 ኪሎሜትር የባህር በር የነበራትና ሁለት ወደቦችንም የምታስተዳደር ሀገር ነበረች ብለዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ እንዳሉት በሀገር ውስጥ በነበረ ቅራኔና የኢትዮጵያን ማደግ የማይፈልጉ የውጭ ጠላቶች ሴራ ምክንያት ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነቷን ከማጣቷም በላይ ወደብ አልባ ሀገር ለመሆን በቅታለች፤ በዚህም ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ተጋልጣለች፡፡

ይህም ባለፉት 30 አመታት የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን ማድረጉን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፣ በየአመቱም ለመወደብ ብቻ ከ፲ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማውጣት እንደተገደደች አስረድተዋል፡፡

ዶክተር አያኖ አክለውም ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ እንዳደረገ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም አሁን ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት ችግሩን በመረዳት ኢትዮጵያን የባህር በር እና ወደብ ባለቤት ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፤ ለዚህም ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት የመንግሥትን ቁርጠኝነት ያሳየ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የሕግና የፖለቲካ መምህር አቶ አወል አሊ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሰረት የሌላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት በለም ላይ ከሚታወቁት ሀገራት አንዷ መሆኗንና አፈጣጠሯም ከውሃ ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚናገሩት አቶ አወል፤ የዓባይ ወንዝ መነሻና በቀይ ባህር ዳርቻ መገኘቷ የዚሁ አመክንዮ ማሳያ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ በአለም እጅግ ተፈላጊ ከሆኑትና የሃያላን ሀገራትንም ቀልብ የሚስብ በመሆኑ እድገቷን የማይፈልጉ አካላት በተቀነባበረ ሴራ ከቀይ ባህር እስኪያርቋት ድረስ ገናና እና በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ ሆና መቆየቷን አቶ አወል ገልጸው፤ ሀገሪቱ ወደብ አልባ ከሆነች ጀምሮ ተፈላጊነቷ ማሽቆልቆሉን ተናግረዋል።

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ መምህር የሆኑት አቶ በፈቃዱ ድሪባ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባህር እንድትወገድ የተደረገበት አካሄድ ምንም አይነት ህጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የህግ ምሁሩ እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባህር እንድትወገድ የተደረገበት መንገድ በአለም አቀፍ ህግ ተቀባይነት የለውም፡፡

አቶ በፍቃዱ እንደሚያስረዱት፤ ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትወገድና ወደብ አልባ እንድትሆን የተደረገው በ1902 እና 1908 ከቅኝ ገዚዎች በተደረጉ ውሎች አማካኝነት ነው፡፡ እነዚህ ውሎች ደግሞ በተባበሩት መንግስታት መሰረታቸውን አጥተዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሲቋቋም ካወጣቸው ድጋጌዎች አንዱ ሀገራት የቅኝ ግዛት ውሎችን የመቀበል ግዴታ እንደሌለባቸው የሚደነግገው አንቀጽ አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ሀገር ካለመሆኗም ባሻገር በቅኝ ገዢዎች የተረቀቁትን የ1902 እና 1908 ውሎችን የመቀበል ግዴታም እንደሌለባት አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ኢትዮጵያ የበርካታ ወደቦች ባለቤትና ፲ሺ800 ኪሎሜትር የሚረዝመውን የቀይ ባህር ጠረፍ ስታስተዳድር መቆየቷን የሚያሳዩ ታሪካዊና ህጋዊ ማስረጃዎች እንዳሉም አመልክተዋል፡፡

ሰሞኑን የኢትዮጵያ መንግስት ከሶማሊላንድ ጋር ያደረገው ስምምነትም ኢትዮጵያውያንን የሚያስደስትና ሰላማችንና አንድነታችንን አስጠብቀን መጓዝ ከቻልን እንደሀገር በርካታ አማራጮች እንዳሉም ማሳያ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

## የጤና መድህንን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ባስተላለፉት መልእክት እንዳሉት፤ የጤና መድህን አገልግሎት ሽፋን እየጨመረ መጥቶ በሚቀጥለው ዓመት ሁሉንም ወረዳዎች ለማድረስ በሚያስችል ቁመና ላይ ይገኛል፡፡

ሽፋኑን ከማሳደግ ባሻገር አተገባበሩ የጤና ሥርዓትን ሀገራዊ አቅም በሚያሳድግ መልኩ እንዲሆን ትኩረት ሰጥተን መሥራት ይኖርብናል ብለዋል፡፡

እስካሁን ትኩረት ተደርጎ የተሠራው ማህረሰብ አቀፍ ፕሮግራም ላይ እንደነበር አስታውሰው፤ ይህንን ማጠናከርና ማስፋት እነደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

እንደሀገር የጤና መድህን ሥርዓቱ የተሟላ እንዲሆን ወደ መደበኛ የጤና መድህን ሥርዓት ፕሮግራም መሸጋገር ይገባል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ሥርዓቱን ለመተግበርም ባለድርሻ አካላትን አስተባብሮ መሥራትን እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል፡፡

የጤና መድህን ሥርዓት ዋናው መርህ የጤናን ሥርዓት ሀገራዊ አቅም ማጠናከር ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብዙዎች በሚያደርጉት መዋጮ ህዝቡ እየተገለገለ የጤና ሥርዓታችንን አቅም እየፈጠረ ይሄዳል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የተሻለ ገቢ ያላቸው ዜጎች ከፍ ያለ ክፍያ እየከፈሉ አነስተኛ ገቢ ላላቸው መደጎም የሚቻልበትን መንገድ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

አባላትን ማስፋትና ዝቅተኛ ገቢ ያቸውን ዜጎች ተደራሽ ማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ እንደሀገር የጤና መድህን ሥርዓት በሁሉም መንገድ የተሟላና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ከሌሎች የልማት አጀንዳዎች ጋር አስተሳስሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከፌዴራል ጀምሮ በተዋረድ ጠንካራ አደረጃጀት መዘርጋት እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

የጤና ሚኒስትሯ ሊያ ታደሰ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የጤና መድህን ሥርዓቱ ጠንካራ ሆኖ ዘላቂነት ያለውና ጥራቱ ተጠበቀ የጤና ሥርዓት ለመዘርጋት አጋዥ እንዲሆን መዋጮው ገቢን መሠረት ባደረገ መልኩ መሰብሰብ እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የጤና መድህን መዋጮው አጠቃላይ የጤና ሥርዓቱን እንዲያግዝ ይጠበቃል ያሉት ሚኒስትሯ፤ አሁን ላይ ያለው ድርሻ አነስተኛ ነው፤ 31 በመቶ የጤና ወጪ በለጋሾች የሚሸፍን ሲሆን መንግሥት የሚሸፍነው 34 በመቶ ነው፡ ፡ የጤና መድህኑ የሚሸፍነው ግን ከአንድ በመቶ የዘለለ አይደለም ብለዋል፡፡

ድርሻውን ለማሳደግ አባላትን ከመጨመር ጎን ለጎን እድሳቱን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር የሚተሳሰርበትን መንገድ ማበጀት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የአገልግሎት ጥራቱን ለማሳደግና የመድሃኒት አቅርቦት ላይ የሚስተዋሉ ችግችን ለመፍታት ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

እስካሁን ድረስ የጤና መድህን ሥርዓትን በመላው ሀገሪቱ በአንድ ሺህ 22 ወረዳዎች መተግበር መቻሉ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ከ55 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የጤና መድህን ሽፋን ተጠቃሚ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡

## የከሠም ስኳር ፋብሪካን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በታች ነው። ይህ የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ደግሞ በቂ የሸንኮራ አገዳ አቅርቦት ባለመኖሩ ነው።

ፋብሪካው ቀን 60ሺ ኩንታል አገዳ በመፍጨት ስድስት ሺህ ኩንታል ስኳር የማምረት አቅም አለው ያሉት አቶ ፈጠነ፣ ሆኖም በሸንኮራ አገዳ እጥረት ምክንያት በሚፈለገው ልክ ለማምረት አለመቻሉን ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል የከሠም ግድብ 500 ሚሊየን ሜትር ኪዩብ ውሀ በመያዝ 20ሺ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ ማልማት እንደሚችል የጠቆሙት አቶ ፈጠነ፣ ፋብሪካው ቢያንስ 12 ሺ ሄክታር የሸንኮራ አገዳ እንደሚያስፈልገውም ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት በራሱ እያለማ ያለው ሶስት ሺ ሔክታር ብቻ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ፈጠነ እንደገለጹት፤ አጠቃለይ ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ እንዲያመርት ለማስቻል በሚቀጥሉት አራት አመታት ለፕሮጀክትና ኢንቨስትመንት ስራ አምስት ቢሊየን ብር ያስፈልገዋል። ገንዘቡን ከልማት ባንክ በብድር ለማግኘት የተጠየቀ ሲሆን ጥናት ተካሂዶ አዋጭነቱ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በኩል እየታየ ይገኛል።

ፋብሪካው በ2004 ግንባታው ተጀምሮ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ለይ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ከ2007 እስከ 2010 ዓም ድረስ የአገዳ አቅርቦቱን ይሸፍን የነበረው ራሱ ከሚያመርተው ሶስት ሺ ሔክታር የሸንኮራ አገዳ ተጨማሪ በአሚባራ ሀላፊነቱ የተወሠነ የግል ድርጅት በስድስት ሺ ሄክታር መሬት ይለማና ይቀርብ ከነበረ አገዳ ነበር ብለዋል።

አሚባራ እርሻ ልማት ከ2010 ዓም ጀምሮ በድርቅ፣ በጎርፍና በሌሎች ችግሮች ምክንያት ከሸንኮራ አገዳ ልማት በመውጣቱ ፋብሪካው ከ 2011 ዓም ጀምሮ ዛሬም ድረሥ በአገዳ እጥረት ሲያመርት ከሚገባው ከአንድ አራተኛ በታች እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብለዋል።

አጠቃላይ ፕሮጀክቱ በቀድሞ መስኖ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ባለቤትነት ሲመራ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ባለመረጋገጡ፤ እንዲሁም በቂ የመሠረተ ልማት ባለመዘርጋቱ ፋብሪካው በራሱ አቅም አገዳ በማልማት ፍላጎቱን መሸፈን ሳይችል ቆይቶ ዛሬ ለደረሠበት ደረጃ በቅቷል ሲሉም አቶ ፈጠነ ተናግረዋል።

ፋብሪካው ሲተዳደር የነበረው በስኳር ኮርፖሬሽን ስር የነበረ ሲሆን ከ2014 ዓም መጨረሻ ጀምሮ ግን በቦርድ እንዲተዳደሩ ከተወሠነላቸው አምስት ስኳር ፍብሪካዎች አንዱ ሆኗል። ይህንንም ተከትሎ በተሠሩ የማስተካከያ ስራዎች ከአሚባራ እርሻ ልማት ጋር ተቋርጦ የነበረው ስራ እንዲቀጥል ውል ተገብቷል ብለዋል።

በግዚያዊነት በውስጥ አቅም የአገዳ ምርት አቅርቦትን ለመጨመር በየሳምንቱ የምርት ዘመቻ እንቅስቃሴ እየተከናወነ ይገኛል፤ ያሉት አቶ ፈጠነ በቀጣይም የመሬት ይዞታውን ለማረጋገጥ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስምምነቱ የሀገራቱን ሕዝቦች የወንድማማችነት ታሪክ በጠንካራ መሠረት ላይ ዳግም የሚያንጽ ነው!

ለውጡን ተከትሎ የተጀመረው መነቃቃት በብዙ ተግዳሮቶች እየተፈተነ፤ ሀገርና ሕዝብን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እያሻገረ ስለመሆኑ በየዕለቱ የምንታዘባቸው ተጨባጭ እውነታዎች ማሳያ ናቸው። አይቻልም “አይታሰብም” የሚሉ የትናንት ትርክተቶችን ሳይቀር ወደ ታሪክነት እየቀየረ እየሄደበት ያለው የቁርጠኝነት መንገድ በርግጥም የጀመርነው የለውጥ ጉዞ በብዙ የከሰርንባቸውን ትናንቶች እንደሚክስን አመላካች እየሆነ ነው።

ሀገርን አበቃላት ከሚል ሟርት ከመታደግ ጀምሮ፤ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ እየሄድንበት ያለው በፈተናዎች የተሞላ መንገድ፤ የቱንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለን ፤ አሁን ላይ እንደ ሀገር እያስመዘገብነው ያለው እመርታ ፤ አዲስ ሀገራዊ ትርክት በመፍጠር መጪው ዘመን የተሻለ እንዲሆን ከሁሉም በላይ የአስተሳሰብ መሠረት የጣለ ነው።

የብዙ ትውልዶችን ብሩህ ተስፋዎች ፤ ያደበዘዙ የትናንት የስህተት መንገዶቻችንን ቆም ብሎ በሰከነ መንፈስ በማየትና በማረም ዘላቂ መፍትሄ በማፈላለግ ላይ የተመሠረተው የለውጡ መንገድ ፤ ችግሮችን በውይይትና በድርድር በሰላማዊ መንገድ የመፍታት አዲስ የፖለቲካ ባህል ለመፍጠር ረጅም ርቀት ተጉዟል። ለዚህም ከፍያለ ዋጋ ለመክፈል የተገደደበት ክስተትም ተፈጥሯል።

ምንም ሳታጣና ብዙ እያላት ላልተገባ ድህነት የተዳረገችውን ኢትዮጵያ፤ ካለችበት ያልተገባ ስፍራ በማውጣት፤ ድህነትን ታሪክ ሊያደርግ የሚችል ብሄራዊ የልማት መነቃቃት በመፍጠርም፤ ዜጎች በነገዎቻቸው ተስፋ እንዲያደርጉ፤ ድህነትን ታሪክ በማድረግ ትግል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን እያደረገ ነው፤ በዚህም እየተገኘ ያለውም ስኬት ዓለም አቀፍ እውቅና እስከማግኘት የደረሰ ሆኗል።

ፋታ የማይሰጡ የሀገር ውስጥ ችግሮች በሚፈራረቁበት፤ ይህንን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የሀገርና የሕዝብን ጥቅም አደጋ ውስጥ የሚከቱ ዓለም አቀፍ ጫናዎች በበዙበት ሁኔታ፤ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ከማስመዝገብ ጀምሮ፤ በችግር ወቅት ሊታሰቡ የማይችሉ የልማት ሥራዎችን በማከናወን የለውጥ አመራሩ ለተነሳበት የለውጥ መንፈስ ያለውን ቁርጠኝነት በተግባር አሳይቷል።

ከፍ ባለ ተስፋ እና የሕዝባችን ርብርቦሽ ተጀምሮ አደጋ ውስጥ የነበረውን የዓባይ ግድብ ፤ ከነበሩበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች በማላቀቅ የመጨረሻ ምእራፍ ላይ እንዲደርስ አድርጓል። ብዛት ያላቸው የቱሪስት መዳረሻዎችን በመገንባት በዘርፉ ያለውን ሀገራዊ አቅም ወደ ሀብት መለወጥ ችሏል። በምግብ እህል ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ተከትሎ በስንዴ ልማት የተገኘውም ስኬት ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘት የቻለ ነው።

ከዚህም ባለፈ ላለፉት ሶስት አስርቶች አይነኬ ሆኖ የቆየውን የባህር በር ጉዳይ ፤ለሀገርና ለሕዝብ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ከፍ ባለ ድምጽ በማሰማት ፤ ሕዝባችንን በጉዳዩ ዙሪያ ከተኛበት እንዲነቃ፤ ዓለም አቀፉም ህብረተሰብ እንደ ሀገር በጉዳዩ ዙሪያ ያለንን አቋም እንዲያውቀው እና ከጎናችን እንዲሰለፍ የሚያስችል ፤ የለውጡን ታሪክ የሚያደምቅ ተግባር ፈጽሟል።

ሀገራችን በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች የሚቆጠሩ የባህር በሮች የነበሯት፤ በተለያዩ የታሪክ ስብራቶች እነዚህን ወደቦቿን አጥታ በአሁኑ ወቅት ወደብ አልባ ብትሆንም፤ ይህንን የህልውናችን ጉዳይ የሆነውን የወደብ ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ ዘመኑን በሚዋጅ የትብብርና የወዳጅነት መንፈስ ዕውን ለማድረግ እየሄደበት ያለውም መንገድ ከተስፋነት ወደሚጨበጥ እውነታነት እየተለወጠ ነው።

እንደ ሀገር ካለን ከፍያለ የሕዝብ ብዛትም ሆነ ከውሃ አካላት ካለን ርቀት አንጻር ነጻና አስተማማኝ የባህር በር የማግኘት መብታችን በዓለም አቀፍ ሕግ፤ ከታሪክ እና ከሞራል አንጻር የሚደገፍ ቢሆንም ፤ ፍላጎቶች አጅግ በበዙበት በዚህ ዘመን በቀላሉ ሊተገበር የሚችል አይደለም፤ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ነገን አሻግሮ ማየትና ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት የሚጠይቅም ነው።

ከዚህ አንጻር መንግሥት ከሁሉም በላይ በእጅ ያሉ ሰላማዊ አማራጮችን በአግባቡ አይቶ እና ለይቶ በማሳየት፤ ከዚህ የሚመነጭ መተማመንና ወዳጅነትን በማጠናከር ፤ ነገዎችን ከኛ አልፈው ለሌሎች ብሩህ ሆነው የሚታዩበትን የአእምሮ ውቅር/የአስተሳሰብ መሠረት / በመገንባትና ይህንንም የአደባባይ እውነት አድርጎ በኃላፊነት መንፈስ መንቀሳቀስ መቻሉ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ትልቅ የስኬት መንገድ ሆኗል።

መንገዱ በአንድም ይሁን በሌላ ለሀገራችን አስተማማኝ እና ቀልጣፋ የወደብ አማራጭ ማቅረብ የሚችሉ ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የተሻለ ዕድል የሚፈጥር፤ እጣ ፈንታቸውን የሚያስተሳስር፤ የመጡበትን የወዳጅነትና ወንድማማችነት መንገድ የበለጠ የሚያጎለብትና የቤተሰብነት መንፈሳቸውን በሁለንተናዊ መንገድ የሚያሳድግ ነው።

ከትናንት በስቲያ ከሶማሌ ላንድ ጋር እንደ ሀገር ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ እና ቀልጣፋ አማራጭ የባህር በር ለማግኘት የደረስንበት የመግባቢያ ስምምነት ፤ ከዚህ እውነት የተቀዳ የሁለቱን ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት መሠረት ያደረገና ለቀጣናዊ ተስስርና ልማት ፈር ቀዳጅ ነው። ከዚህ ባለፈ የሁለቱን ሀገራት ሕዝቦች እጣ ፈንታ የሚያስተሳስርና የቀደመውን የወንድማማችነት ታሪካቸውን በጠንካራ መሠረት ላይ ዳግም የሚያንጽ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአንዳችን ችግር፤የሁላችንም ችግር ነው

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የሰው ልጅ መቼም በምድር ላይ እየኖረ የመጥፎ እና ጥሩ ዕድሎች መመላለሻ ሃዲድ ነው፡፡ መልካም ዕድሎች ሲመጡ ዝም ብለው የሚመጡ ሳይሆኑ ለዚህ የሚሆኑ መደላድሎች በመፈጠራቸው ነው። መጥፎ ዕድሎችም የሰው ልጅ የእሳቤ ውጤት ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እንደ ሀገርም የሚከሰቱ ጥሩ ይሁኑ መጥፎ ክንውኖች የዜጎችና የመንግሥታት የጋራ ውጤቶች ናቸው፡፡

እንደ ሀገር ችግር ሲመጣ ለጊዜው የተወሰነውን ቡድን ወይንም ማህበረሰብ ብቻ ለይቶ የሚጎዳ ይመስላል፡፡ ከዚህ የተነሳ አያገባኝም የሚል ብዙ ሊሆን ይችላል፤ ቆይቶ ግን ችግሩ ሁሉንም የሚያገባው ይሆናል፡፡ የአንዱ ችግር የሁሉም ችግር፤ የሁሉም ችግር ደግሞ የአንዱ ችግር ሆኖ መፍትሄውም ችግሩም የእሽክርክሪት ጨዋታ ይመስል እዚያው በዚያው ይሆናል፡፡

ይህን ሃሳብ የበለጠ ለማብራራት አንቂ መፅሃፍት ገፆች ከሚል የማህበራዊ ድረ ገጽ የወሰድኩትን ፅሁፍ ላጋራችሁ፡፡ ‹‹በአንድ ገበሬ ቤት የምትኖር አይጥ ነበረች። ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን ይህችው አይጥ ገበሬው እና ባለቤቱ እቃ ሸምተው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ትመለከትና ለእኔ የሚሆን ምን ገዝተው ይሆን? ብላ በቀዳዳ አጮልቃ ስታይ ፍፁም ያልጠበቀችው ነገር ትመለከታለች፡፡ የተገዛው ነገር የሚበላ ሳይሆን የአይጥ ወጥመድ ነበር፡፡

‹‹በድንጋጤ ውስጥ እንዳለች ከጉድጓዷ ወጥታ እየሮጠች በጊቢው ውስጥ ወዳሉት የቤት እንስሳት ሄደች፡፡ መጀመሪያ ያገኘችው ዶሮን ነበር፤ እየጫረች ጥራጥሬ ስትለቅም። ‹‹ማነሽ አንቺ ዶሮ፣ ኧረ! ጉድ አልሰማሽ፣ ቤት ውስጥ ወጥመድ ተገዝቷል።›› ብትላት ጊዜ ዶሮዋ እየተቆናጠረች ‹‹እና ምን ይጠበስ! አንቺ ተጨነቂበት እንጂ እኔን የሚያሳስበኝ ነገር አይደለም›› አለቻት፡፡

‹‹አይጧ እየተበሳጨች ወደ በግ ሄደችና ‹‹ስማኝማ! አቶ በግ፣ ቤት ውስጥ ወጥመድ ተገዝቷል፤ እባክህ አንድ ነገር እናድርግ›› ስትል በተማፅኖ ብጠይቀውም በጉ ካቀረቀረበት ሣር ላይ ቀና ሳይል ‹‹በጣም ያሳዝናል! ግን ልረዳሽ አልችልም፤ ራስሽ ተወጪው›› አላት፡፡

‹‹አሁንም አይጥ ቁና ቁና እየተነፈሰች፣ ወደ በሬ ዘንድ ሄደችና ቤት ውስጥ ስለተገዛው ወጥመድ ነገረችው፡፡ በሬውም ምንም ሳይመስለው እንዲህ ሲል መለሰላት፣ ‹‹እንዲያው ምን ይሻልሻል? ባይሆን በግ እና ዶሮ ይርዱሽና አንድ ነገር አድርጊ፤ እኔን እንኳን ተይኝ አላት፡፡

‹‹አይጧ ተበሳጭታ፤ ‹‹ኧረ ተው! ተው! አንድ ነገር ብናደርግ ይሻላል፤ ለጊዜው ቢመስላችሁም ችግሩ የጋራችን ነው›› ስትል ተናገረች፡፡ ሁሉም ተያይተው ተሳሳቁባት። ‹‹ቀልደኛ ነሽ!›› እየተባባሉ። አይጥም ተስፋ ቆርጣ ወደ ጉድጓዷ ገብታ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ሳይወስዳት አደረች፡፡

‹‹ማታ ወጥመዱ ተጠምዶ እያለ ቀጭ የሚል ድምፅ ሲሰማ የገበሬው ሚስት ተስፈንጥራ ተነሳች፤ ወጥመዱ የያዛትን አይጥ ለማየት። ጨለማ ስለነበር በዳበሳ ወደ ወጥመዱ ሄዳ ወጥመዱን ስትነካው በአይጥ ፋንታ የተያዘው መርዘኛ እባብ ስለነበረ ነደፋት፡፡

‹‹በነጋታው የገበሬው ሚስት ከሐኪም ቤት ስትመለስ ራስ ምታት እንዳያስቸግራት ተብሎ ዶሮዋ ታረደችና ሾርባ ተዘጋጀላት፡፡ የገበሬው ሚስት ህመሙ እየጠናባት ሲሄድ በቶሎ እንድታገግም ተብሎ በግ ታረደላት፡፡ ሆኖም ግን ሴትዮዋ ማገገሟ ቀርቶ ሞተች፡፡ ይህንን ተከትሎ ዘመድ አዝማድ ለለቅሶ ሲመጣ ለተስካር በሚል በሬውም ታረደ። የሚገርመው አይጥም ቁጭ ብላ እያለቀሰች ሦስቱም ሲታረዱ አየች።

እንደ ሀገር የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ እንደመሆናችን፤ በብዙ ተግዳሮቶች እየተፈተንን ነው። ከነዚህ ውስጥ የሠላም ጉዳይ በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ዜጎች ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሰቀው ለመስራት ብዙም ነፃነት እየተሰማቸው አይደለም፡፡

አሁን አሁን ከኢትዮጵያዊ እሴትና ባህል በእጅጉ ያፈነገጡ ወንጀሎች እና ፀያፍ ድርጊቶች እየተፈፀሙ ስለመሆናቸው መስማት እየተለመደ መጥቷል፡፡ የሠዎች እገታ፣ መፈናቀልና ኢ-ሠብዓዊ የሆኑ ድርጊቶች፤ በእነዚህ ችግሮች ላይ ደግሞ የኑሮ ውድነት ዜጎችን ምሬት ውስጥ እየከተተ ነው፡፡

ዜጎችን በማገት ከፍተኛ ገንዘብ ከሚጠይቁት ኢ-መደበኛ ኃይሎች እና ፀረ ሠላም አካላት ጨምሮ እራሳቸውን በተለያየ መንገድ አደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኛ ኃይሎች እንደ ሀገር ተፈጥረው የነበሩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም፤ የልብ ልብ እየተሰማቸው እውነታውም መከሰቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

እርግጥ ነው፤ ‹‹ውፍረት እና ስህተት ለባለቤቱ አይታየውም›› የሚባል ብሂል አለ። እነዚህ አካላት አሁን ስህተቱ አይታያቸውም፤ በእነርሱ አተያይ ትክክል ናቸው፡፡ የበለጠ ትክክል ነን የሚያስብላቸውን ዕድል ደግሞ ሕዝቡ የሰጣቸው ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ገና እነዚህ ልምምዶችን ሲጀምሩ እረፉ! አድቡ! የሚላቸው ማህበረሰብ መኖር ነበረበት። አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ለእነዚህ አካላት ከለላ የመስጠት ዝንባሌ መኖሩ መንግሥትም ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዳይወጣ እንቅፋት ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ነገሩን ገና ከመነሻው መግታት ቢቻል፤ ከመሠረቱ ፈር ቢይዝ፤ ዛሬ የሚታዩ እኩይ ተግባራት ቦታ ባልነበራቸው ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን አልረፈደም፤ ችግሩ የጋራ ነው፤ መፍትሄውም መተመሳሳይ የጋራ ነው የሚል እሳቤ ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የአይጥ እና የሌሎች እንስሳት ታሪክ ለአሁናዊ ችግሮቻችን ሆነ ለቀጣይ ብዙ ልንማርበት የሚገባ ነው። እንስሳቱ ገና ከጅምሩ ችግሩ ሁሉም ይመለከተናል ቢሉ ኖሮ ባላለቁ ነበር፡፡ ‹‹ያልጠረጠረ ተመነጠረ›› እንዲሉ አበው፤ ነገሮችን ከተለመደው መንገድም ወጣ ባለ ሁኔታ መቃኘት አሊያም መመልከት ይገባል፡፡

በሀገር ላይ የተደቀነ አደጋን በክብደቱ መጠን ልንመለከተው የሚገባ ነው። የሀገር ጉዳይ የሀገር ነው፤ የሁላችንም ነው፡፡ የሀገር ጉዳይን የሆነ አካል ወይም ቡድን ጉዳይ አድርገን ልንመለከተው አይገባም። በዚያ መልኩ ማየት ከጀመርን የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እንደሞኙ በግ፣ እንደ ቸልተኛው በሬ እና እንደ ሆድ አደሯ ዶሮ ከመበላት አናመልጥም፡፡ አይጧ እንዳለችው… ‹‹ለጊዜው ቢመስልም፤ ለኔ የመጣ ጢስ ላንቺ አይመለስም›› ነው ነገሩ፡፡

ከዚህ የተነሳ ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ የማህረሰብ አንቂዎች፣ የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ በአንድም ይሁን በሌላ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ አካላት ሆነ ማንኛውም ዜጋ እዚህ ሀገር በሚከሰቱ ችግሮች ዙሪያ በኃላፊነት መንፈስ በጋራ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ ውጪ ሀገራዊ ችግሮችን ለተወሰነ አካል ሰጥቶ እጅን አጣምሮ መቀመጥ ሆነ ችግሮችን በማራገብ የሚመጣ ዘላቂ መፍትሄ አይኖርም፡፡

## ፍረዱኝ


# የቀበሌው ንግድ ቤት ኪራይ ውዝግብ - በመርካቶ

ሙሉቀን ታደገ እና ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የዛሬው «የፍረዱኝ ዓምድ» ዝግጅታችን በመዲናችን አዲስ አበባ የተፈጠረን አንድ ውዝግብ ያስመለክተናል። ውዝግቡ የተፈጠረው በቀድሞው የመጠሪያ ስሙ ዞን አንድ ወረዳ 5 ቀበሌ 06 በአሁኑ መጠሪያው ደግሞ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 በተለምዶ መርካቶ ይርጋ ኃይሌ ዙሪያ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፤ ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 በተለምዶ መርካቶ ይርጋ ኃይሌ ዙሪያ እየተባለ በሚጠራው ሰፈር የንግድ ቤት ቁጥር 1004 የሆነውን የቀበሌ ቤት ተከራይ ናቸው። እናም ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ፣ «በውል እና ማስረጃ የገዛሁትን እንዲሁም ከወረዳ 08 የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቶኝ በራሴ የጉልበት እና የገንዘብ ወጪ የገነባሁትን፤ የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ሳከናውንበት የነበረን የቀበሌ ቤት ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ በወረዳ 8 አመራሮች ተነጥቂያለሁ፡፡ ሕዝብን እንዲያገለግሉ መንግሥት ባስቀመጣቸው ሹመኞች የደረሰብኝን በደል ተመልክቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፍረደኝ» ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ዝግጅት ክፍል አቤት አሉ።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ቡድንም የባለጉዳዩዋን ቅሬታ አድምጦ፤ ሰነዶችን አገላብጦ እና የሚመለከታቸውን አካላት አናግሮ፤ በጥቅሉ ስለጉዳዩ ከሰዎች እና ሰነድ ያገኛቸውን መረጃዎች እና ማስረጃዎች በጥልቀት መርምሮ የደረሰበትን ውጤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ግራና ቀኙን አይቶ መፍረድ ይችል ዘንድ እነሆ ብሏል፤ መልካም ንባብ፡፡




**ይህን ተከትሎ ምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ቦታው ድረስ በመሄድ ሁኔታውን ከተመለከተ በኋላ «ሴፕቲክ ታንከሩ ካልተሰራ የአቤቱታ አቅራቢዋ ድርጅት መሥራት አይችልም» ብሎ ቤቱን ዘጋ**

### ከአቤቱታ አቅራቢዋ አንደበት

"በደል ተፈጸመብኝ" ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን አቤቱታ ያቀረቡት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ እንደሚናገሩት፤ ውዝግብ የተነሳበት ቤት በዓዋጅ 47/67 የተወረሰ ሲሆን፤ ቤቱም ለንግድ አገልግሎት የሚውል ነው። በዚህ ቤት ከ1968 ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 1987 ዓ.ም ድረስ አቶ ሰይፉ አርጋው የተባሉ ግለሰብ የንግድ ሥራ ያከናውኑበት ነበር፡፡

በመስከረም ወር 1987 ዓ.ም ድንገት በተፈጠረ የእሳት አደጋ ምክንያት ቤቱ ወደ ዓመድነት ተቀየረ። ይህን ተከትሎ በቦታው ላይ ግንባታ ለማከናወን የገንዘብ አቅም ያጡት አቶ ሰይፉ የቤቱን ቁልፍ ለወይዘሮ ሙሉ ሸጡ፡፡ ወይዘሮ ሙሉም ባዶ ቦታውን የገዙት ወደፊት አልምተው ለመጠቀም ባላቸው ተስፋ ነው፡፡

ቤቱን ገዝተው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በአካባቢው ሌባ ይበዛበት እንደነበር የሚናገሩት ወይዘሮ ሙሉ፤ በወቅቱ ንብረታቸውን ተዘርፈው ባዶ እጃቸውን የቀሩ በርካቶች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ አካባቢው ያልለማ እና የቆሸሸ ስለነበርም ዘመዶቻቸው እና የቅርብ ጓደኞቻቸው ቦታውን እንዳይገዙት መክረዋቸው እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቦታው ወደፊት የሚኖረውን ተፈላጊነት በማጤን እንደገዙት ይናገራሉ፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙሉ ገለጻ፤ ምንም እንኳን ወዳጅ ዘመዶቻቸው ቦታውን እንዳይገዙ ያላደፋፈሯቸው ቢሆንም፤ እርሳቸው ግን በቦታው ላይ ሰርቶ የመለወጥ ከፍ ያለ ሕልም ስለነበራቸው ሕልማቸውን ለማሳካት ከባንክ ብድር ወስደዋል። ይሄም አልበቃ ሲላቸው ከግለሰቦች በአራጣ እስከመበደር ደርሰዋል፡፡ በወቅቱ 200 ሺህ ብር የሚገመት ገንዘብ ወጪ አድርገዋል፡፡ የተቃጠለውን ቤት ቁልፍ ግዥ ሲፈጽሙም ሁሉም የግዥ ሂደት የተከናወነው በውል እና ማስረጃ ነበር፡፡

አቶ ሰይፉ፣ የንግድ ሥራ ሲያከናውኑበት የነበረውና በመስከረም ወር 1987 ዓ.ም የተቃጠለው ቤት የጭቃ እና ከእንጨት የተሰራ ነበር የሚሉት ወይዘሮ ሙሉ፤ የቤቱን ቁልፍ ከአቶ ሰይፉ ከገዙት በኋላ የግንባታ ፈቃድ ከወረዳ 8 በማውጣት ቤቱን በብሎኬት መሥራታቸውን ገልጸዋል፡፡ በወቅቱ የተሰጣቸው የግንባታ ፈቃድም በርካታ ቤቶችን መሥራት እንዲችሉ የፈቀደ ስለነበር ቤቱን ሲገነቡ ሁለት ዓይነት የንግድ ሥራ ማከናወን የሚያስችል አድርገው መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙሉ ማብራሪያ፣ በዚህ መሠረት አንደኛው ክፍል የመኝታ/አልጋ ቤት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሲሆን፤ በመኝታ ቤቶቹ ዙሪያ የተሰሩት ደግሞ የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦችን ለመሸጥ የሚያስችሉ ሱቆች ነበሩ፡፡ የግንባታ ፈቃዳቸው የሰጣቸውን እድል ተጠቅመውም ወይዘሮ ሙሉ በቤቱ (በቤት ቁጥር 1004) ሁለት የንግድ ፈቃድ አወጡ፡፡ አንደኛው ቤት የመኝታ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ብትን ጨርቅ ለመሸጥ የሚውል ነበር፡፡

ይሄን ተከትሎም ሥራውን ሊያግዛቸው ገበያቸውን ሊያሰፋላቸው የሚችል ሰው ስላስፈለጋቸው፤ የልብስ ቤት ፈቃድ ባወጡባቸው ቤቶች ጨርቅ እንዲያሻሽጡላቸው በማሰብ ከመርካቶ አካባቢ የነበሩ የተወሰኑ ልብስ ሰፊዎችን በነጻ በቤታቸው ውስጥ እንዲሰፉ ይፈቅዱላቸዋል፡፡ በወቅቱ ልብስ እንዲያሻሽጡላቸው የተፈቀዱላቸውን ግለሰቦች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰፉ የመረጧቸው ልብስ ሰፊዎች ደግሞ ብዙ ደንበኛ ያላቸው ነበሩ፡፡

እንዳሰቡትም ሥራውን በጀመሩበት ጊዜ የንግድ ሥራቸው በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነበር፡፡ በሁሉም ሱቆች ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኝ የንግድ ሥራ እያከናወኑ ነው በሚልም በመንግሥት ከፍተኛ ግብር ተጥሎባቸው በዚያ ወቅት እስከ 60ሺህ ብር መክፈል ችለውም ነበር።

በወቅቱ በጨርቅ መሸጥ እና የመኝታ አገልግሎት በመስጠት የተሰማሩት ወይዘሮ ሙሉ «ጥምር ንግድ» በሚል ፈቃድ ተሰጥቷቸው ነበር። ግብርም የከፈሉት የጥምር ንግድ ሥራ በሚል ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ግን በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ ጨርቅ እንዲያሻሽጡላቸው ሲንጀር የልብስ ስፌት ማሽን ይዘው ከንግድ ቤታቸው ያስጠጓቸው ሰዎች በራሳቸው የገንዘብ እና የጉልበት ወጪ የሰሩትን ቤት በተለይም የጨርቃጨርቅ ፈቃድ አውጥተው ይሰሩባቸው የነበሩባትን ቤቶች እንዲወርሱ ተደረገ፡፡

እዚህ ጋ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ግን፣ በወቅቱ ለጨርቃ ጨርቅ ሽያጭ ተብሎ የተለየው አንድ ቤት ዘጠኝ ቦታ የተሸነሸነ እንጂ፤ እነዚህ የተከፋፈሉት(ሽንሽን) ክፍሎች ራሳቸውን ችለው የተሰሩ አይደሉም፡፡ በአንድ ቤት ውስጥ ያሉ ሌሎች ትናንሽ ክፍሎች ነበሩ፡፡

በኋላም ወይዘሮዋ ቅሬታ ስላቀረቡ፣ ከተነጠቁት ሽንሽን ቤቶች መካከል አንድ ቤት ተሰጣቸው፡፡ የተሰጣቸውን አንድ ክፋይ ክፍል 1004/ለ የሚል ስያሜ ሰጧት፡፡ ይሄን የተመለከቱት ወይዘሮ ሙሉም ይህ ለምን ይሆናል? እንዴት በአንድ ቤት ሁለት የቤት ቁጥር ይሰጣል? ብለው ቢጠይቁም ሰሚ አላገኙም። አሁንም ድረስ «ከተሸነሸኑት ዘጠኝ ጠባብ ቤቶች የተሰጣቸው ቤት 1004/ለ መባሉ አግባብ አይደለም። እንዴት በአንድ ቤት ሁለት ቁጥር ይሰጣል?» ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ደግሞ፣ ምንም እንኳን በዚህ መልኩ ክፍሎቹ የተወሰዱባቸው ቢሆንም፣ እነዚህ ክፍሎች የሰሩት ቤት አንድ አካል ስለሆኑ ኪራይ የሚከፈሉት ራሳቸው ወይዘሮ ሙሉ ናቸው፡፡ ክፍሎቹን መነጠቃቸውም ሆነ በተነጠቋቸው ክፍሎች ኪራይ መክፈላቸው ትክክል አለመሆኑን የሚናገሩት ወይዘሮ ሙሉ፤ ሌላው ቢቀር የተነጠቋቸው ክፍሎች (የተቀነሱት ቤቶች) ስፋት ተሰልቶ የቤት ኪራይ ሊቀነስ፤ ካልሆነም ክፍሎቹ ሊመለሱላቸው እንደሚገባ ቅሬታቸውን አስረድተዋል፡፡

አሁን ላይ ወይዘሮ ሙሉ ኪራይ ለሚከፍሉባቸው ቤቶች፣ 1004 እና 1004/ለ ብሎ ሁለት የቤት ቁጥር የተሰጣቸው ናቸው፡፡ በዚህም አቤቱታ ወይዘሮ ሙሉ ሁለት የንግድ ፈቃድ እንዲያጡ ተደርገዋል፡፡ ይህም ሕግን ያልተከተለ ከመሆኑ በሻገር፣ የግለሰቦችን የመሥራት ሞራል የሚጎዳ ነው በማለት ስለ ሁኔታው አስረድተዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙሉ ገለጻ፤ የድርጅቱ (የንግድ ቤታቸው) ሴፕቲክ ታንከር የተገነባው በወረዳው ከተወሰዱባቸው ስምንት ቤቶች የግንባታ መሠረት ሥር ነው፡፡ ይህ ሴፕቲክ ታንከር ባለፈው ጊዜ ፈንድቶ አካባቢውን በማወኩ የአካባቢው ማኅበረሰብ ወይዘሮ ሙሉን ከሶ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ ምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ቦታው ድረስ በመሄድ ሁኔታውን ከተመለከተ በኋላ «ሴፕቲክ ታንከሩ ካልተሰራ የአቤቱታ አቅራቢዋ ድርጅት መሥራት አይችልም» ብሎ ቤቱን ዘጋ፡፡ ወይዘሮ ሙሉም ሥራቸውን ቶሎ ለመጀመር በማሰብ ሁለት መቶ ሺህ ብር አውጥተው ሴፕቲክ ታንከሩን ማሰራታቸውን ይገልጻሉ፡፡

### ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎች

ከላይ በቀረበው አግባብ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰውን የወይዘሮ ሙሉ ቅሬታ መነሻ በማድረግ የመልካም አስተዳደር እና የምርመራ ዘገባ ቡድኑ በርካታ ሰነዶችን ለመመልከት ጥረት አድርጓል። በዚህም ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ በምርመራ የተገኙ ሰነዶች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሰነዶች መካከልም የተወሰኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

**ሰነድ አንድ፡-** የክልል 14 መስተዳደር በቁጥር ክ14/ዞ1/ከኛ3ለ/ሰ-11/28/87 በቀን 26/04/87 የጻፈው ደብዳቤ ነው፡፡ ይሄ ደብዳቤ፤ በክልል 14 መስተዳደር ዞን 1 ወረዳ 5 ቀበሌ 06 በተከራይ አቶ ሰይፉ አራጋው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# የቀበሌው ንግድ ቤት ኪራይ...

**ከገጽ 6 የዞረ**

ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ቁጥር 1004 የሆነ የቀበሌ ቤት ቀደም ብሎ ከነበረው ቤት የተሻለ አድርጎ ለመገንባት ተከራዩ አዲስ ግንባታ አቀማመጥ ንድፍ በማቅረብ የግንባታ ፈቃድ እንዲፈቀድላቸው መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህን ተከትሎ የቀረበው ንድፍ ተቀባይነት በማግኘቱ ቤቱ በአቶ ሰይፉ አርጋው እና በወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ ስም እና ፊርማ የብሎኬት ቤት መገንባት እንደሚችሉ ፈቃድ የሰጠ ነው። በዚህ የግንባታ ፈቃድ አሁን ላይ ወይዘሮ ሙሉ የተወሰዱባቸው ቤቶች «ተለጣፊ ክፍሎች» በሚል የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው እንደነበር ተመላክቷል፡፡

**ሰነድ ሁለት፡-** በክልል 14 መስተዳደር የወረዳ 5 ቀበሌ 06 መስተዳደር ጽህፈት ቤት በቁጥር 1589/መ15/ወ5/ቀ06/88 በቀን 24/9/88 በጻፈው ደብዳቤ ነው፡፡ በዚህ ደብዳቤ ደግሞ፤ አቶ ሰይፉ አርጋው የተባሉ ግለሰብ የቤት ቁጥር 1004 የሆነውን ድርጅታቸውን ለወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ ኅዳር 28 ቀን 1988 ዓ.ም ባቀረቡት የሽያጭ ውል መሠረት በክልል ፍርድ ቤት ውል ክፍል ቀርቦ የጸደቀላቸው ስለመሆኑ እና አቶ ሰይፉ ይጠበቅባቸው የነበረውን ግብር ከፍለው በማጠናቀቃቸው ባስገቡት የሽያጭ ውል መሠረት ድርጅቱ ወደ ወይዘሮ ሙሉ እንዲዞር መደረጉን የሚገልጽ ሃሳብ ሰፍሯል፡፡

በዚህ ደብዳቤ እንደተመላከተው፤ ወይዘሮ ሙሉ የውል ማዘዋወሪያ ገንዘብ በደረሰኝ ቁጥር 565921፣ 10ሺህ ብር ከፍለዋል፡፡ ይህን ተከትሎም ቀደም ሲል በአቶ ሰይፉ አርጋው ስም ኪራይ ሲከፈልበት የነበረው የቀበሌ ንግድ ቤት ወደ ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ ዞሮ ወይዘሮ ሙሉ በቤቱ ኪራይ መክፍል እንደሚችሉ የቀበሌው ሥራ አስፈጻሚ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡


**ሰነድ ሶስት፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብ መድኃኒት፣ ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ጽህፈት ቤት በቀን 09/11/2010 ዓ.ም እና በቁጥር አ/ከ/ከ/ከ/ም/መ/ ጤክ/አ/ቁ/0442010 ለወይዘሮ ሙሉ በጻፈው ደብዳቤ ነው፡፡ ይሄኛው ደብዳቤም፣ በወረዳ 08 በወይዘሮ ሙሉ ሀረገወይን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ቁጥር 1004 የንግድ ሥራ የሚካሄድበት የድርጅት ቤት መሆኑን ገልጾ፤ ከድርጅቱ የሚወጣው የፍሳሽ ቆሻሻ የአካበቢውን ማኅበረሰብ ጤና እየጎዳ በመሆኑ ከተገቢው አካል ፈቃድ በመውሰድ በሰባት ቀናት ውስጥ ሴፕቲክ ታንከር በመገንባት የፍሳሽ ቆሻሻውን እንድታስወግዱ የሚል ነው፡፡

### የወረዳ 08 ምላሽ

የቅሬታ አቅራቢዋን አቤቱታ በመያዝ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመልካም አስተዳደር እና ምርመራ ክፍል የጋዜጠኞች ቡድን፣ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 ሥራ አስፈፃሚ የሆኑትን አቶ አሰፋ ዩጂ፣ ስለጉዳዩ የሚያውቁትን እንዲያስረዱ፤ መፍትሔ የሚሉትንም እንዲገልጹ ጠይቋል፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ ለቀረበላቸው ጥያቄም ምላሽ የሰጡት ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደሚሉት፤ ወይዘሮ ሙሉ ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ ቅሬታቸውን በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ ነበር፡፡ እንደ ወረዳ አመራርም ይህን ጉዳይ ጠንቅቀው ያውቁታል። ግለሰቧ በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያቀርቡ በነበረው ቅሬታ መነሻነትም ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ የሚመለከታቸው አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች ጉዳዩን ቦታው ድረስ ወርደው ተመልክተውታል፡፡

እንደ አቶ አሰፋ ገለጻ፣ በ2004 ዓ.ም በወጣው የቤቶች መመሪያ መሠረት እንደ ወረዳ የተወሰደው ርምጃ ትክክለኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ወይዘሮ ሙሉ የያዙት ሁለት የመንግሥት ቤት ነው፡፡ አንደኛው ትልቅ ሆቴል ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ኤሌክትሮኒክስ አክሰሰሪ መሸጫ ነው፡፡ በመሆኑም በመመሪያው


የአዲስከተማክፍለከተማአስተዳደርምግብመድሃኒትጤና
ክብካቤአስተዳደርና
ቁጥጥር ጽ/ቤት
Addis ketema sub city administration food,medicine
Health care administration and control
office

**ቁጥር** አ/ከ/ከ/ክ/ም/መ/ጤ/ክ/አ/ቁ/044/2010
ቀን 09 / 11 /2010

ለ ወ/ሮ ሙሉ ሐረግወይን
አዲስአበባ

**ጉዳዩ፡-ማስጠንቀቂያ መስጠትን ይመለከታል**

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረዉ በወ/ሮ ሙሉ ሐረግወይን ስም ተመዝግቦ በወረዳ 08 የቤት ቁጥር 1004 ያለ እና በአካባቢዉ የሬስቶራንትና የሻወር አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ከድርጅቱ በሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻ አካባቢን እየበከለ ነዉ በሚል የአካባቢዉ ነዋሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ከጽ/ቤታችን ባለሙያዎች ልከን የችግሩን ሁኔታ በቀን 06/11/2010 የታየ ሲሆን በወቅቱም የሻወር ቤት ፍሳሽ ቆሻሻ አካባቢዉን መበከሉን ለማየት ችለናል።

ይሄ ደሞ የም/መ/ጤ/ክ/አ/ቁ/ጽ/ቤት አዋጅ ላይ የተጠቀሰዉን ማንኛዉም ከአንድ ድርጅት የሚወጣ ፍሳሽ ወደ ወንዝ ወይም ሌላ አካባቢን በሚበክል ሁኔታ ማስወገድ ከመስሪያቤታችን ድንብ ጋር ስለሚፃረር ድርጅታችሁ በ07 ቀናት ዉስጥ ከተገቢዉ አካል ፍቃድ አዉጥቶ ሴፕቲክ ታንከር በመገንባት የፍሳሽ ቆሻሻችሁን እንድታስወግዱ እያልን ችግሩ ለዘለቄታዉ መፍትሄ እስከ ሚያገኝድረስ የታሸጉት 07 ሻወር ቤቶችና አንድ መፀዳጃ ቤት ታሽገዉ ይቆያሉ፡፡

« ከሰላምታ ጋር »
አብርሃም ግርማ
የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ባለሙያ

➤ ለአዲስ ከተማ ክ/ከ/ም/መ/ጤ/ክ/አ/ቁ/ጽ/ቤት

መሠረት አንደኛው ቤት ለመንግሥት፣ ሌላኛው ደግሞ ለግለሰቧ የሚቀር ይሆናል፡፡ በዚህ አሰራር ደግሞ በርካቶች ተገዥ ሆነዋል፤ ወይዘሮ ሙሉ ግን ይህን ተግባራዊ ለማድረግ አልፈለጉም፡፡ በመሆኑም ወረዳው የሚጠበቅብንን ማድረግ ነበረበት፤ ያንኑ አድርጓል፡፡

ምክንያቱም፣ ወረዳው ዘንድ ያለው መረጃ ወይዘሮ ሙሉ የፈረሙት ሁለት ውል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አንደኛ ቤት የማይገባቸው በመሆኑ ለመንግሥት እንዲተላለፍ ማድረግ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ሆኖም የግለሰቧ ፍላጎት ከሆቴላቸው ውጭ ያሉትን ዘጠኝ መደቦችን አጠቃለው መያዝ ነው፡፡ ይህን ግን ወረዳው መፍቀድ አይችልም፡፡ ከዚህም ባሻገር ወረዳው በቀሪዎቹ ቤቶች (ክፍሎች) ላይ ከሌሎች ህጋዊ አካላት ጋር ውል ተዋውሏል፡፡

‹‹እኛ እንደ ወረዳ ምንም የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር አልፈልግም›› ያሉት አቶ አሰፋ፤ ዘጠኙን ሱቆች መንግሥት የወረሳቸውም ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ ከመንግሥት ጋር ውል ፈፅመው ራሳቸው አሳልፈው ለሌሎች ያከራዩዋቸው በመሆኑ ነው፤ ይህ ደግሞ አግባብነት የጎደለው እና ከሕግ አንጻር የተከራይ አከራይ ሆነው የተገኙ በመሆኑ ሕጋዊ ርምጃ ለመውሰድ ተገደናል ብለዋል፡፡ ይህን የፈጸምነውም በመመሪያ እንጂ በራሳችን ፍላጎት ወይንም በጥቂት ግለሰቦች ይሁንታ አይደለም ሲሉ ስለሁኔታው አስረድተዋል፡፡

ቀደም ሲል ወይዘሮ ሙሉ ከመንግሥት ጋር ውል የገቡት የኪራይ ውል 1004 በሚል በተመዘገበው የቤት ቁጥር ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ቤቱን እንዴት ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› ተብሎ ለሁለት ተከፈለ? የሚለውን አቶ አሰፋ ሲያስረዱም፤ ቤቱ ቀደም ሲል አንድ ሊሆን ይችላል። ይሁንና ወይዘሮ ሙሉ ቤቱን ለሁለት ይከፈልልኝ፤ ቁጥርም ይሰጠው ብለው በማመልከታቸው ለቤቱ ሁለት ቁጥር ተሰጥቶታል ነው ያሉት፡፡

አቶ አሰፋ አያይዘውም፣ ወይዘሮ ሙሉ ቤቱ ሁለት ቁጥር እንዲሰጠው የጠየቁበት ማመልከቻ በአቤቱታ አቅራቢዋ እናት ማህደር ውስጥ ስለመገኘቱ የገለጹ ሲሆን፤ ይሄንን የማመልከቻ ሰነድ ግን ማቅረብና ለገለጻቸው አስረጅ አድርገው ለጋዜጠኞች ማሳየት አልቻሉም፡፡

ይሄም ቅሬታ አቅራቢዋ (ወይዘሮ ሙሉ) ያለፍላጎታቸው እና በማያውቁት ሁኔታ ቤቱ ለሁለት መከፈሉን ሲያስረዱ ለነበረውን ጉዳይ ወረዳው በማስረጃ ላይ ተመስርቶ ለዝግጅት ክፍላችን መመለስ ያልቻለ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም፤ አቶ አሰፋ ግን፣ ወይዘሮ ሙሉ ሁለት ውል እና ሁለት የቤት ቁጥር ይዘው በማግኘታችን አንዱን ቤት ለመቀበል መገደዳቸውን ይገልጻሉ፡፡

አቶ አሰፋ፣ ሕጋዊ የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የተገነቡ ቤቶችን ከአቤቱታ አቅራቢዋ የተነጠቁበትን ምክንያት ሲያስረዱም፤ ቤቱን የተነጠቁት ለሶስተኛ ወገን አከራይተው በመገኘታቸው መሆኑን ገልጸዋል። ይህን ተከትሎ ዝግጅት ክፍላችን ቅሬታ አቅራቢዋ ቤቱን ለሶስተኛ ወገን ያከራዩበት የሰነድ ማስረጃ አላችሁ? ሲል አቶ አሰፋን የጠየቀ ሲሆን፤ የአቶ አሰፋ ምላሽ "አዎ! የሰነድ ማስረጃ አለን" የሚል ነበር። ሆኖም እንደ ቀድሞው ሁሉ ለዚህኛው ሃሳባቸው ደጋፊ የሆነ የሰነድ ማረጋገጫ (ግለሰቧ ቤቱን ያከራዩበትን ውል የሚያሳይ ሰነድ) ማቅረብ ሳይችሉ ቀሩ፡፡

ሌላው ከቤቶቹ መተላለፍ ጋር ተያይዞ የተነሳው ጉዳይ የሴግቲ ታንከር ጉዳይ ነው፡፡ ይሄም ወይዘሮ ሙሉ በቅሬታቸው የግንባታ ፈቃድ አውጥተው በአዲስ መልክ ቤቱን ሲገነቡ ለሆቴሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ‹‹ሴፍቲ ታንከር›› ከሱቆቹ ሥር መገንባቱን መናገራቸው ነበር፡፡ ዝግጅት ክፍሉም የወይዘሮ ሙሉ የሆቴላቸው ቆሻሻ ማስወገጃ/ ማጠራቀሚያ ሴፍቲ ታንከር ላይ ያረፉት ሱቆች ወይም መደቦች ለሌላ ተላልፈው መሰጠታቸው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሴፍቲ ታንከሩን ለአደጋ ማጋለጥ እና ኅብረተሰቡንም አደጋ ላይ መጣል አይሆንምን? የሚለውን ጉዳይ አቅርቦ ነበር፡፡

ምክንያቱም ወይዘሮ ሙሉ ለዝግጅት ክፍሉ ባቀረቡት ቅሬታ ወቅት፣ የሴፍቲ ታንከሩ ጉዳይ ቀደም ሲል በሥራቸው ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑን በመጠቆም፤ አሁንም መሰል ችግር ቢፈጠር ማን ሊጠየቅ ነው? ይሄንን በተደጋጋሚ ጠይቄ ሊሰማኝ የቻለ አካል የለም፤ ታዲያ በቀጣይ ለሚፈጠሩ ችግሮች ኃላፊነቱን የሚችል አካል ማን ነው? የሚሉ ጭምር ነበሩ፡፡

ቀደም ሲልም በዚሁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ‹‹ሴፍቲ ታንከር›› የጤና እክል በመፍጠሩ የወረዳው የጤና ባለሙያዎች ይህን በማረጋገጣቸው እና ችግር ፈጥሯል በመባሉ የገንዘብ ቅጣት መቀጣታቸውን፤ በሌላ መልኩ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ‹‹ሴፍቲ ታንከር›› ሌላ ቦታ ይገንባ ቢባል እንኳን ቦታ አለመኖሩን በመጠቆም፤ ችግሩ ውስብስብ መሆኑንና ግድየለሽ ውሳኔዎች እየተወሰኑ እንደ ግለሰብም ሆነ ተብሎ በደል እየደረሰባቸው መሆኑን ደግሞ ለዚህ ሥጋታቸው እንደ ምክንያት አስረድተው ነበር፡፡

አቶ አሰፋ ግን፣ ወይዘሮ ሙሉ ስለ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ‹‹ሴፍቲ ታንከር›› እስካሁን ቅሬታ አላቀረቡም፤ ይህ አዲስ ስልት ሊሆን ይችላል፡፡ ቤቱ በአዲስ የተገነባው 1987 ዓ.ም ነው፡፡፡ ያም ቢሆን እኔ የሚመለከተኝ ግንባታው እንዴት እና መቼ ተከናወነ የሚለው አይደለም፡፡ ጉዳዩ ዛሬ ለምን በአዲስ ሁኔታ ማንሳት አስፈለገ የሚለውን ማሰብ ይገባል፡፡ ሆኖም ይህ ቅሬታ እውነት ከሆነ እኛ እንደ አስተዳደር የምንመለከተው ጉዳይ ሊኖር ይችላል፤ እንደ አስፈላጊነቱም መፍትሔ ለመስጠት ጥረት እናደርጋለን ሲሉ ስለ ጉዳዩ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም፣ "እኔ የምመለከተው ውሉን ነው፡፡ በእጃቸው ላይ ስንት ቤት አለ የሚለውን ማጣራት ነው፡፡ መመለስ የሚጠበቅብኝ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለት ቤት ውል መዋዋላቸውን በማጣራታችን የተወሰደ ርምጃ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፤" በማለትም የወሰዱት ርምጃ የጋራ መገልገያዎችን ማዕከል በማድረግ ሳይሆን ግለሰቧ ሁለት ቤት የመያዛቸውን እውነት ማዕከል ያደረገ ስለመሆኑም ገልጸዋል፡፡

ስለቤቱ 1997 ዓ.ም የሲ.አይ.ኤስ መረጃን፣ እንዲሁም የእርሳቸውን ምልከታ አስመልክቶ እንዲያብራሩ በተጠየቁት መሠረትም ሥራ አስፈጻሚው በሰጡት ምላሽ፤ በዚህ ላይ መረጃዎች አሉ፤ በግልጽም ተቀምጧል፡፡ ይሁንና 1997 ዓ.ም የሲ.አይ.ኤስ መረጃዎችን ከወይዘሮ ሙሉ ፋይል ውስጥ ማግኘት አልተቻለም፣ ሲሉ አስረድተዋል። ከመመሪያው ጋር በተያያዘም፣ መመሪያውን ተከትሎ አንድ ቤት ሁለት እና ከዚያ በላይ መሸንሸን እንደሚቻል፤ ወይዘሮ ሙሉም በዚህ አግባብ የሚስተናገዱ፤ ለዚህም መመሪያው እንደሚደግፋቸው ተናግረዋል፡፡

ያለ ምክንያት የምንሰራው ሥራ የለም የሚሉት አቶ አሰፋ፤ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ በምንሰራው ሥራም ልንታገዝና ልንበረታታ ይገባል እንጂ ልንወቀስ አይገባም ይላሉ፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት መደቡን/ ክፍሎቹን ሕጋዊ አካላት ባሉበት አሽገነዋል፤ በቀጣይ ግን በሕጉ መሠረት ሱቆቹን ወይንም መደቡን ለሌላ አካል አስተላልፈን ውል እንዋዋላለን ብለዋል፡፡

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 08 የቤቶች የይዞታ ክትትል ባለሙያ የሆኑት አቶ ንጉሴ ገብረ በበኩላቸው፤ ወይዘሮ ሙሉ ወይንሀረግ አሁን እያቀረቡ ያሉት ቅሬታ ከ12 ዓመታት በፊት መፈታት የነበረበት ጥያቄ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

አሁን ላይ የጉዳዩ መነሳት አግባብ አይመስለኝም የሚሉት አቶ ንጉሴ፤ ግለሰቧ እስከ ዛሬ ዝምታ መርጠው መቆየታቸው በጉዳዩ የተስማሙ እንጂ ተቃውሞ ያላቸው አያስመስልም፡፡ ቅሬታም ካላቸው እስከ ዛሬ መቀመጥ አልነበረባቸውም፡፡ ይህ ውሳኔ የተወሰነው በደመነፍስ ወይንም በግለሰቦች ፍላጎት ሳይሆን በወቅቱ ከገነቡት የተወሰኑትን ሱቆችን ለሌሎች አካላት አከራይተው በመገኘታቸው አከራይ ተከራይ መመሪያ መሠረት ቤቱን ተወርሰዋል፡፡ በ2004 ዓ.ም የወጣው አከራይ ተከራይ መመሪያም መሠረትም ወይዘሮ ሙሉ አሁን የሚጠይቁትን መብት ተነጥቀዋል፤ ሲሉ ጉዳዩን አስረድተዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ስምምነቱ ኢትዮጵያ ለጋራ ጥቅም ከጎረቤቶቿ ጋር ለመሥራት ያላትን ፍላጎት በተጨባጭ ያሳየ ነው

**ታምራት ተስፋዬ**

የአፍሪካ ቀንድ ከመልከዓ ምድራዊ፣ ጂኦ-ፖለቲካዊ፣ ስትራቴጂካዊ ፋይዳው አንፃር ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ፣ ዲፕሎማሲና የጸጥታ ተለዋዋጭነት ያስተናግዳል፡፡ የኃያላን ሀገራት ጣልቃ ገብነት ጎልቶ ይታይበታል፡፡ የኢትዮጵያ መገኛም በዚሁ የተጨነቀ ቀጠና መሃል /nucleus / ውስጥ ነው፡፡

የዚህ የፖለቲካ ድባብና ሁኔታም ሀገሪቱም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ይነካካታል፡፡ ቀጠናው ላይ የተለኮሰ እሳት ኢትዮጵያንም ይጠብሳታል፡፡ ከጥንት እስከ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ መስተጋብር የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማዕከላዊ መሠረቶች ወይንም /determinant/ ዋነኛው ይህ ቀጠና ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዚህ ውጥረት ለአፍታም በማይለየው ቀጠና ውስጥ ጥበብ በተሞላበት መልኩ ብሔራዊ ጥቅምን አስጠብቃ ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ ይህ ስኬታማነቷ በአንዳንድ ተመራማሪዎች ዘንድ ዋነኛ ጥያቄ ሆኖ እንደ ትላንቱ ሁሉ ዛሬም ቀጥሏል፡፡

ኤድሞንድ ኬለር የተባሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ‹‹The Politics of State Survival: Change and continuity of Ethiopian Foreign Policy›› በሚለው ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ እንዳመላከቱት፣ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የሀገሪቱን ህልውና ለማስጠበቅ ትልቁ መሳሪያና ጥበብ ነው፡፡

በርግጥም በዚህ ቀጠና በተለያዩ ጊዜያት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚፈትኑ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ ክስተቶች ቢስተዋሉም ፤ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ በሳል የዲፕሎማሲ ክንውኖችን ስታደርግ ቆይታለች።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በመልካም ጉርብትና፣ ሰጥቶ መቀበል፣ በጋራ ተጠቃሚነት፣ በሌሎች ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት፣ የጋራ ደህንነት እና ሌሎች የዓለም አቀፍ ግንኙነት ወርቃማ መርሆች የሚመራ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ቀጠናውን አስመልክቶ የምታራምደው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በጋራ ልማት፣ ተጠቃሚነትና ትብብር ላይ የተመሠረተ መሆኑን በግልፅ የሚታይ ነው። የሀገሪቱ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ዲፕሎማሲ ብልህ የሆነ ሀገራዊ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ነባሬዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

ከጋራ ተጠቃሚነት ማዕከሉን ያደረገ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ጎረቤቶቿን ጭምር የሚጠቅምና የቀጠናውን ሁኔታ መቀየር በሚችል መልኩ የተቃኘ ነው፡፡ የተለያዩ የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ ባልተረጋጋና ውጥንቅጡ በወጣ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ ሀገራት ሁለንተናዊ ማለትም ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ (maximizing its security) መሥራት ግድ ይላቸዋል፡፡ ራሳቸውን በማጠናከር፣ የውስጥ አቅማቸው ከውጫዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም በማድረግ ለውጫዊ ሁኔታው ምላሽ የሚሰጡበት አቅጣጫ ሁሌም ማማተርን መዘንጋት የለባቸውም፡፡

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ሕዝቦች ጋር የሚያስተሳስሯት ጠንካራ የባህል፣ የንግድ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ በመልከዓ ምድር፣ በሃይማኖት፣ የቋንቋ እና የታሪክ ሰንሰለት አላት፡፡ ይህን ከግምት ባስገባ መልኩ ሀገሪቱ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማዳበር በተለይም የሕዝብ ለሕዝብ ጨምሮ የተለያዩ የትስስር ዲፕሎማሲ መንገዶችን እያራመደችም ትገኛለች፡፡

የጎረቤት ሀገራት ዜጎች በኢትዮጵያ የትምህርት፣ ስልጠናና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ማድረግም የዚህ አንዱ ማሳያ ነው። በሺዎች የሚቆጠሩ ኤርትራ፣ የሶማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን ተማሪዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አስፈላጊው ትብብር ተደርጎላቸዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጎረቤት ሀገር ስደተኞችን በመቀበል ስመ ገናና ናት፡፡

ከቀጠናው ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት በሰላምና ደህንነት፣ በንግድ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስኮች ይበልጥ በማጥበቅ ላይ ትገኛለች። በኢኮኖሚ ትስስር ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና በመተግበር አፍሪካን በተለይም ምስራቅ አፍሪካን ለማስተሳሰር እየተጋች ትገኛለች፡፡

በዚህም መሠረት ከጅቡቲ የሚያገናኛት የባቡር ሃዲድ ገንብታለች፡፡ ከሱዳንን ጋር ለመገናኘት የየብስ ትራስፖርት ሥራ ጀምሯል። ኢትዮጵያን ኬንያን የሚያገናኝ የየብስ ትራንስፖርት ሌላኛው የትስስር ገመድ ነው። በእርስ በእርስ መስተጋብር በኢኮኖሚ ትስስር በተለይ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ከጅቡቲ፣ ኬንያና ሱዳን ጋር እየሰራች ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ ከጅቡቲ የወደብ አገልግሎቶችን ስታገኝ፣ ከሱዳን ጋር ደግሞ በነዳጅ ዘይት ግዢ ትገናኛለች፡፡ ይህ ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር (interdependence) በማስፈን አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋግፎ ነገዎቹን ብሩህ የሚያደርግበት፣ የጋራ ተጠቃሚነት ዋነኛው የዲፕሎማሲያ መርህ ያደረገ ስለመሆኑ በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በሁሉም መስፈርት ትልቅ ሀገር ነች፡፡ የሚያሳዝነው ግን ከዓለም የባህር በር/ ወደብ ከሌላቸው ሀገሮች በሕዝብ ብዛት አንደኛ ነች፡፡ ሀገሪቱን ከቀይ ባህርና ከወደብ ባለቤትነት ለመግፋት ከውስጥም ከውጭም የተሰራው ደባና ሴራ ሁሌም ቢሆንም ትውልድን የሚያስቆጭ ነው፡፡

ወደብ ለአንድ ሀገር ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካው እድገት ወሳኝ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለከፍተኛ ኢኮኖሚ ባለቤት የሆኑ ሀገራት በሙሉ የወደብ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ከድህነት አረንቋ ውስጥ ለመውጣት መተንፈሻን ማስፋት የግድ ነው። ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤትነት መሆን ባለመቻሏ ኢኮኖሚው ከፉኛ ታፍኖ ቆይቷል፡፡

ኢትዮጵያ ከወራት በፊት ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድና በጋራ የመልማት መርህን በተከተለ መልኩ በወደብ የመተሳሰር ጥያቄን ማቅረቧም የሚታወስ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ ወደብ ያስፈልጋታል የሚለውን ጉዳይ በተለያዩ መድረኮች ሲያነሱ ያላመኑ፤ ከንቱ ቅዠት የመሰላቸውና ይልቁንም ሀገሪቱን ወደ ጦርነት ሊወስዷት እንደሆነ ስጋት ያደረባቸው ብዙዎች እንደነበሩ የሚታወስ ነው፡፡

ይሁንና በርካቶች መረዳት ያልቻሉት፤ አሊያም ተረድተው መቀበል ያልፈለጉት የዲፕሎማሲ አማራጭ ከቀናት በፊት አሸናፊ ሆኖ ታይቷል፡፡ ከቀናት በፊት ኢትዮጵያን ሶማሊያ-ላንድ ታሪካዊ የተባለ ትስስርን ፈጥረዋል፡፡ ሁለቱ ሀገራትም በወደብ ልማት በጋራ ለመሥራትና በጋራ ለማደግ ከስምምነት ደርሰዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሶማሊላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ ታሪካዊ ነው የተባለውን የመግባቢያ ሠነድ ተፈራርመዋል፡፡

ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበትን የመግባቢያ ስምምነት የሀገሪቱንን መጻኢ ዕድል የሚያሳምር ከመሆኑም በላይ፤ ለዓመታት ወደብ አልባ ለሆነው ሕዝብ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው። የተገኘው የባሕር በር የኢትዮጵያን ስብራት የጠገነና የትውልድን የዘመን ቁጭት የመለሰ ነው።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት ያደረገችው የትብብርና አጋርነት ስምምነት ሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ጡንቻ መፈርጠም ያለው አስተዋጽኦ ነጋሪ የሚያሻው አይደለም። የኢትዮጵያን በሳል የዲፕሎማሲ ውጤት ምስክር ነው፡፡ ይህ ስምምነት ኢትዮጵያ መንግሥት በሰጥቶ መቀበል መርህ እና ለጋራ ጥቅም ከጎረቤቶች ጋር የመሥራት ፍላጎትና አቋምን መልሶ የሚያፀና ነው።

> **አንድ መታወቅ ያለበት ሀቅ ቢኖር ኢትዮጵያ የባሕር በር ብታገኝ የሚጎዳው አካል የለም፡፡ የኢትዮጵያ ፍላጎትም በጋራ ማደግ፣ በጋራ መበልፀግ፣ በጋራ ደህንነትን ማስጠበቅ መሆኑን መረዳት የግድ ነው**

አንድ መታወቅ ያለበት ሀቅ ቢኖር ኢትዮጵያ የባሕር በር ብታገኝ የሚጎዳው አካል የለም፡፡ የኢትዮጵያ ፍላጎትም በጋራ ማደግ፣ በጋራ መበልፀግ፣ በጋራ ደህንነትን ማስጠበቅ መሆኑን መረዳት የግድ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የዓባይ ወንዝን በተለይም ግድቡም በሚመለከት የምታራምደው አቋም ከዚህ በተለየ መነፅር የሚታይ አይደለም።

ምንም እንኳን ወንዙ ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ቢሆንም ሀገሪቱ ሀብቱን በብቸኝነት ልጠቀም የሚል አቋም አሳይታም አታውቅም፡፡ ወደፊትም አታሳይም፡፡ ድንበር ተሻጋሪ ሀብቶች የጋራ መሆናቸውንና ታሳቢ ባደረገ መልኩ አጠቃቀሙም በተለይም ጎረቤት ሀገራትን በሚጠቅምና የጋራ ተጠቃሚነትን እውን በሚያደርግ መልኩ መሆን እንዳለበት በማመን በፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህ ዲፕሎማሲዋን እየመራች ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፍላጎትና የዲፕሎማሲ አቋም የማንንም ብሔራዊ ጥቅም የማይጎዳ ይልቁንም የጋራ ተጠቃሚነት ያስቀደመ መሆኑን ሁሉም ሊረዳ ይገባል፡፡ እንደ ወደቡ ሁሉ የግድቡን ጉዳይም ከጋራና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲሁም የአብሮነት ብልጽግና አንፃር መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡

# ንግድና ግብይት

# ለገበያ ማረጋጋትም የዋለው የአርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋም

**ፍሬሕይወት አወቀ**

እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት እንዲሁም እንደ ሀገር በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረት መንግሥት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሰፋፊ ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆን፣ በእነዚህም ምርትና ምርታማነት በየዓመቱ እየጨመረ ይገኛል። በተለይ በመስኖ እየለማ ያለው ስንዴ ምርት እየጨመረ ያለበት ሁኔታም ይህንን ያመለክታል፡፡

ምርትና ምርታማነት የማሳደጉ ሥራ በገጠር ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ በከተማ ግብርናም እየተሰራበት ነው፡፡ በተለይ በሌማት ትሩፋት ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ መንግሥት በከተሞች መስፋፋት ምክንያት በከተማ ዳርቻ የሚገኙ አርሶ አደሮችን መልሶ በማቋቋም የግብርና ሥራቸውን መቀጠል እንዲችሉ በማድረግ እና ለገበያ ማረጋጋቱ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ትርጉም ያለው ሥራ እየሠራ ነው፡፡

ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ሥር የተቋቋመው የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል እያከናወናቸው የሚገኙ ተግባራት ማሳያዎች ናቸው፡፡

ከማዕከሉ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው፤ ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከተማ ኮዬ ፈጬ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፤ በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችን ያቀፈ ነው፡፡ አርሶ አደሮቹን መልሶ ለማቋቋም የተገነባው ይህ ማዕከል ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን አንግቦ ይሠራል፡፡ አንደኛው ዓላማ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ማቋቋምና ማሻገር ነው፡፡ በመሆኑም መንግሥት ለአርሶ አደሩ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ተከታትሎ ወደ መካከለኛ ኢንቨስትመንት እንዲሸጋገር ያደርጋል፡፡

ሁለተኛው ዓላማ ገበያን ማረጋጋት ነው፡፡ በዚህም የማዕከሉን ምርቶች ለሸማቹ ማኅበረሰብ በማቅረብ ገበያውን የማረጋጋት ሥራ ይሠራል፡፡ በዚህም አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ ወደ ሥራ ከገባ ስምንት ወራትን ያስቆጠረው ይህ የእንስሳት ልማትና የልህቀት ማዕከል በአሁኑ ወቅት በአምስት የሥራ ዘርፎች ማለትም በወተት ልማት፣ በከብቶች ማደለብ፣ በእንቁላል ጣይ ዶሮ እርባታ፣ በእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ዘርፎች አርሶ አደሮቹ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በልማት ምክንያት የተነሱ አርሶ አደር ቤተሰቦች ተደራጅተው በግቢ ውስጥ በተገነቡ የመሸጫ ሱቆች በሽያጭ ሥራ የተሰማሩበት ሁኔታም የልማቱ ዘርፍ ነው፡፡

በማዕከሉ ተደራጅተው ወደ ሥራ የገቡት አርሶ አደሮች 550 የሚደርሱ ናቸው:: እነሱም 150 አባላት በወተት ከብቶች እርባታ፣ 100 በማደለብ፣ 110 በዶሮ እርባታ፣ 30 በመኖ ማቀናበር እና 160 አባላት ከአምራቾቹ ምርቶቹን ተቀብለው በማዕከሉ መግቢያ በር በተዘጋጁ ሱቆች በመሸጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ የአርሶ አደር ቤተሰቦች ይገኙበታል። እነዚህ የአርሶ አደር ቤተሰቦች በማዕከሉ የሚመረተውን እንቁላልና ወተት ተረክበው በአካባቢው ለሚገኙ ነዋሪዎች፣ ለኅብረት ሥራ ማህበራትና ለመንግሥት ሠራተኞች በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ከማቋቋም ባለፈ ገበያን በማረጋጋት ጉልህ አበርክቶ ያለው የእንስሳት ልማትና የልህቀት ማዕከሉ የእንቁላል እና የወተት ምርትን በተለይም እንቁላልን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ በማቅረብ ገበያውን እያረጋጋ ይገኛል። የዝግጅት ክፍላችንም ወደ ማዕከሉ ባቀናበት ወቅት ከሸማቾችና ከአምራቾቹ መረዳት የቻለው ይህንኑ ነው።

በማዕከሉ መግቢያ ግራና ቀኝ ላይ ከተደረደሩት የወተትና የእንቁላል መሸጫ ሱቆች መካከል እንቁላል መሸጫ በሆነው አንደኛው ሱቅ እንቁላል እየገዛች ያገኘናት ወይዘሪት ሜላት ዓለሙ፣ በማዕከሉ አቅራቢያ ከሚገኘው የኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ መንደር ነዋሪ ናት፡፡

ሜላት በተደጋጋሚ ወደ ማዕከሉ በመምጣት እንቁላል ትገዛለች፡፡ በአካባቢው ከዚህ ቀደም አንድ እንቁላል ከ12 እስከ 16 ብር ድረስ ሲሸጥ እንደነበረ አስታውሳ፣ ማዕከሉ ተገንብቶ ሥራ ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ግን አንድ እንቁላል በስምንት ብር እየገዛች መሆኑን ገልጻለች፤ እንዲህ ዓይነት ማዕከላት በከተማዋ ያለውን የኑሮ ውድነት በማቃለል ገበያን ማረጋጋት እንደሚችሉ አስረድታለች፡፡

ሜላት እንዳለችው፤ እንዲህ ዓይነት ማዕከላት በየአካባቢው ቢኖሩ አሁን ላይ ያለውን የኑሮ ውድነት ማረጋጋት ይቻላል፡፡ መንግሥት በዚህ ዙሪያ በተለይም በከተማ ግብርና እየሠራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ነው፡፡ በተለይም በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ እንዲህ ዓይነት ለሕፃናት ጠቃሚና ገንቢ የሆኑ የእንቁላልና የወተት ምርቶች ነጋዴው እጅ ሳይገቡ በቀጥታ ከአምራቹ ማግኘት መቻሉ በራሱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለመጪዎቹ በዓላትም ምርቱ በተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ ቢሆን መልካም መሆኑን ጠቁማለች፡፡

**ማዕከሉ እንቁላል በስፋት እያመረተ ለገበያ በማቅረብ ከተማ ውስጥ ያለውን የእንቁላል ዋጋ ማረጋጋት ችሏል፡፡ አንድ እንቁላል በስምንት ብር፣ አንድ ሊትር ንጹህ የላም ወተት ደግሞ በ70 ብር እየሸጠ ይገኛል። አንድ ሰው በቀን እስከ 20 እንቁላል ከማዕከሉ መግዛት ይችላል**

ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ ብሩህ ፋና ዩኒየን የመጣችው ወይዘሮ ሐረግ መኮንን በበኩሏ በክፍለ ከተማው ሥር ለሚገኙ ዩኒየኖች የእንቁላል ምርት ለመግዛት እንደመጣች አጫውታናለች፡፡ እሷ እንደምትለው፤ ዩኒየኑ በኅብረት ሥራ ኤጀንሲ በኩል ከማዕከሉ 25 ሺ እንቁላል በየሳምንቱ መውሰድ ይችላል፡፡ በክፍለ ከተማው 11 ወረዳዎች እንዳሉ ጠቅሳ፣ ይህን አቅርቦት ለሁሉም በአንድ ጊዜ ማዳረስ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ዩኒየኑ በየሳምንቱ በመመላለስ በተራ ያዳርሳል ብላለች፡፡

የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት በተለያየ ስፍራ የሚገኙ ናቸው፤ ሱቅ ያላቸው፣ መዝናኛ ክበብ ያላቸውና በእሑድ ገበያ የሚያቀርቡ በመሆናቸው ዩኒየኑ በቅድሚያ ፍላጎት ሰብስቦ በቀን ለአምስት ወረዳዎች ከአራት ሺ እስከ አምስት ሺ እንቁላሎችን ያቀርባል፡፡

የሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የገለጸችው ወይዘሮ ሐረግ፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት ያለውን የኑሮ ውድነት ከማረጋጋት አንጻር ከማዕከሉ በተጨማሪ ዩኒየኖች አበረታች ሥራ እየሠሩ ነው ብላለች፡፡ ማህበራቱ በተለይም እንቁላልን ጨምሮ ጤፍ፣ ዱቄትና የጽዳት ዕቃዎችን ጭምር በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅበረሰቡ በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ሥራ እየሠራ መሆኑን ገልጻለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ በተለይም ማዕከሉ ከተከፈተ ጊዜ ጀምሮ አንድ እንቁላል በስምንት ብር በመግዛት ማህበራቱም የትራንስፖርት ወጪያቸውን በሳንቲም ቤት ጨምረው ለማኅበረሰቡ እያቀረቡ ይገኛሉ። ከተማ ውስጥ 16 ብር ደርሶ የነበረው የእንቁላል ዋጋም በአሁኑ ወቅት እየወረደ እንደሚገኝና በመደበኛው ገበያ እስከ 12 ብር እየተሸጠ መሆኑን አመላክታለች፡፡

በማዕከሉ ከሚገኙ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት አባላት ካላቸው 11 የዶሮ እርባታ ሼዶች በአንዱ አቶ ጌትነት ፍቃዱ ይሰራሉ፡፡ አቶ ጌትነት፤ የልማት ተነሺ የአርሶ አደር ቤተሰብ ሲሆኑ፣ የመጡትም ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ነው፡፡ ቄብ ዶሮዎችን ይዘው ወደ ማዕከሉ በመምጣት ለሁለት ወራት ቀልበዋቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ዶሮዎቹ እንቁላል መስጠት ጀምረዋል፡፡

እሳቸው ያሉበት ማህበር 3ሺ200 ዶሮዎች እንዳሉት የጠቀሱት አቶ ጌትነት፤ በቀን እስከ 2ሺ100 እንቁላል እያገኙ ናቸው፡፡ በሳምንት ሶስት ቀናትም እንቁላሉን በማዕከሉ ለሚገኙ የሽያጭ ሠራተኞች ያቀርባሉ፡፡ እንቁላሉን የሚያስረክቡት በማዕከሉ ግቢ ውስጥ ለተደራጁ ማህበራት ሲሆን፣ አንድ እንቁላል በሰባት ብር ያስረክባሉ፡፡ ማህበራቱም በሰባት ብር የተረከቡትን እንቁላል በስምንት ብር ለሸማቹ ያቀርባሉ፡፡ ይህም አሁን ያለውን የኑሮ ውድነት በማረጋጋት ረገድ ትልቅ አበርክቶ እንዳለውና ገበያውን ማረጋጋት ችሏል ብለው እንደሚያምኑም ገልጸዋል፡፡

ማህበሩ በቀጣይ እንቁላል ከማምረት በተጨማሪ ወደ ዶሮ ሥጋ የመሸጋገር እቅድ እንዳለው የጠቀሱት አቶ ጌትነት፤ በዶሮ እንቁላል ልማቱ ላይ በሚገባ ልምድ አዳብረዋል፡፡ ሌሎችን ማስተማርና ማሰልጠን እንደሚችልም ተናግረዋል። ማዕከሉ የልማት ተነሺ ለሆኑ አርሶ አደሮች የሥራ ዕድል በመፍጠሩ መደሰታቸውን ገልጸው፣ ማኅበረሰቡም በተለይም የእንቁላልና የወተት ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንስሳት ልማትና የልህቀት ማዕከል ሥራ አስኪያጅ አቶ ታደሰ ተስፋዬ እንዳሉት፤ ማዕከሉ የከተማ ግብርና በማስፋት ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል። በ11ዱም ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ የማቋቋም ሥራ እየተሰራ ነው። አርሶ አደሮችን መልሶ ከማቋቋም ባለፈ ገበያ በማረጋጋትም እንዲሁ ትርጉም ያለው ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ማዕከሉ በስድስት ክፍለ ከተሞች ሥራውን ተግባራዊ ማድረግ ችሏል፡፡ እነሱም የካ፣ ቦሌ፣ ለሚ ኩራ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶና ኮልፌ ቀራኒዮ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን መልሶ ማቋቋም ተችሏል፡፡

በአሁኑ ወቅትም እንቁላል፣ ወተትና የደለቡ በሬዎች በማዕከሉ የሚገኙ ስለመሆናቸው ያነሱት አቶ ታደሰ፤ በተለይም እንቁላል በስፋት እያመረተ ለገበያ በማቅረብ ከተማ ውስጥ ያለውን የእንቁላል ዋጋ ማረጋጋት ችሏል ነው ያሉት፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አንድ እንቁላል በስምንት ብር ሲሸጥ ንጹህ የላም አንድ ሊትር ወተት በ70 ብር ይሸጣል። አንድ ሰው በቀን እስከ 20 እንቁላል መግዛት ይችላል፡፡ ምርቶቹን ለነጋዴዎች አይሸጥም፤ በተለይም በበዓላት ወቅት እንቁላል ተፈላጊ በመሆኑ ለመጪዎቹ የገና እና የጥምቀት በዓላት በበቂ ሁኔታ ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

ወደ ማዕከሉ መጥተው መግዛት ለማይችሉ የማኅበረሰብ አካላትም እንዲሁ የገበያ አማራጭ ያላቸው ሲሆን፤ በዩኒየኖች አማካኝነት በየክፍለ ከተማው ለማኅበረሰቡ እንዲቀርብ እየተደረገ ነው:: ወደ ሌሎች የማኅበረሰቡ አካላት ለመድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመሥሪያ ቤታቸው የሠራተኞቻቸውን ዝርዝር አቅርበው እንቁላል በስምንት ብር ማግኘት ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ሠራተኛም አንድ ትሪ እንቁላል መውሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእሑድ ገበያና በበዓላት ወቅት በባዛርና ኤግዚቢሽኖች ላይ ምርቶቹን ያቀርባል፡፡

የማዕከሉ ግንባታ አንደኛውና ሁለተኛው ተጠናቅቆ ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም፣ ሶስተኛው ምዕራፍ አሁን ያለውን ያህል ግንባታ እንደሚጠይቅ ጠቅሰዋል። ማዕከሉ ወደፊት በቀን መቶ ሺ እንቁላል የማምረት ዕቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅት በማዕከሉ የሚገኙ 36 ሺ ዶሮዎች በቀን እስከ 28 ሺ እንቁላል እየጣሉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በመልሶ ማቋቋም የተደራጁ አርሶ አደሮች በመንግሥት ድጋፍ የሚደረግላቸው መሆኑን ያነሱት አቶ ታደሰ፤ በቅድሚያ ለግብርና ሥራቸው መነሻ ገንዘብ 50 በመቶ በቀጥታ ይሰጣቸዋል። 50 በመቶውን ደግሞ ከወለድ ነጻ በሆነ መንገድ ብድር ያመቻችላቸዋል፡፡ ይህንን ድጋፍ ያገኙ አርሶ አደሮችም በተሰማሩበት የግብርና ዘርፍ እየሠሩ ውጤት ማስመዝገብ የቻሉ ሲሆን፤ በየዕለቱ ለገበያ ከሚያቀርቡት እንቁላልና የወተት ምርቶች የሚያገኙትን ገቢ ቆጥበው የሚከፍሉ ይሆናል፡፡

ከእንቁላልና ወተት በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው የደለቡ በሬዎች ለመጪዎቹ ሁለት በዓላት የተዘጋጁ መሆናቸውን እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ እንደሚቀርቡ የጠቆሙት አቶ ታደሰ፤ የደለቡ ከብቶች በዓመት ውስጥ እስከ ሶስት ጊዜ እንደሚያቀርብ አስታውቀዋል። ወተትም እንዲሁ በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ ለአካባቢው ማኅበረሰብ በሊትር 70 ብር ሂሳብ እየቀረበ መሆኑን ጠቁመዋል፤ ማኅበረሰቡ ወደ ማዕከሉ በመምጣት የእንቁላል፣ የወተትና የደለቡ ከብቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገዛም ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ሥር የተቋቋመው የእንስሳት ልማትና የልዕቀት ማዕከል በ140 ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ ግንባታው በሶስት መርሃ ግብር ተከፋፍሎ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት አንደኛውና ሁለተኛው የግንባታ መርሃ ግብር ተጠናቅቆ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ በቀጣይም ሶስተኛው የግንባታ መርሃ ግብር ሲጠናቀቅ ማዕከሉ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስፋትና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

# በገና ጨዋታ ስምን ጌቶች አልተቆጡም?

**ዋስልኝ አየለ**

‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› የሚለው የእረኞች ጨዋታ ሲወርድ ሲወራረድ መጥቶ አሁን በምሑራን እና ትልልቅ ታዋቂ ሰዎች ጭምር የሚታወቅ የሥነ ቃል ግጥም ሆኗል፡፡ እንዲህ የገና በዓል በመጣ ቁጥር ደግሞ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የማስታወቂያ ማድመቂያ ሆኗል፡፡ ግን ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› የተባለው ለምን ይሆን?

የራሱ የሆነ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ወይም ሌላ ትውፊታዊ ትርጓሜ ይኖረው ይሆናል፡፡ በገጠሩ አካባቢ በእረኞች ዘንድ ግን ለምን እንዲህ እንደሚባል የማውቀውን ላስታውስ፡፡

በተለይም በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የታኅሣሥ ወር የበጋ ወቅት መጀመሪያ ነው፡፡ ይህ የበጋ ወቅት ደግሞ የመኸር ሰብል ተሰብስቦ የሚገባበት ነው፡፡ የመኸር ሰብል መሰብሰቡ ለእረኞች ትልቅ እፎይታ ነው፡፡ ምክንያቱም የመኸር ሰብል ማሳ ላይ ባለበት ወቅት ከብት እንዳያበላሸው እረኞች ከብቶችን ይጠብቃሉ፡፡ በዚህን ወቅት ከብት ወይም ፍየል አምልጦት እህል ያስበላ እረኛ በቤተሰቦቹ ወይም በእህሉ ባለቤት ሊገረፍ ይችላል፤ መገረፉ ቢቀር እንኳን ኃይለኛ ቁጣ ያጋጥመዋል፡፡

እነዚህ እረኞች የበልግ ወቅት ከሆነ ከሚያዚያ እና ግንቦት ጀምሮ፣ ያ ቢቀር ግን ከሰኔ ወር ጀምሮ ለግማሽ ዓመት ያህል የእረኝነት ሥራ ላይ ይጠመዳሉ። በክረምትም ሆነ በመኸር ወቅት ከብቶች ቡቃያ እና ሰብል እንዳይበሉ ይጠብቃሉ፡፡ እረፍት የሚያገኙት ከታኅሣሥ እስከ ሰኔና ግንቦት ድረስ ባሉት ወራት ነው፡

በዚህ ምክንያት የገና በዓል ለገጠር እረኞች ልክ እንደ አውሮፓና አሜሪካ ሀገራት በሉት፡፡ የፌሽታና የደስታ ወቅት ነው፡፡ አውሮፓውያን አዲስ ዓመት ስለሚመጣላቸው፣ የኢትዮጵያ ገጠራማ እረኞች ደግሞ እረፍት ስለሚያገኙ እና ከአቻዎቻቸው ጋር ለረጅም ጊዜ የገና ጨዋታ ስለሚወጫወቱ፡፡

የገና በዓል በበዓልነቱ የዝናውን ሚና ወሰደ እንጂ ለገጠር እረኞች የገና ትልቁ ደስታ የገና ጨዋታው ነው፡፡ ይህ ጨዋታ የገና ዕለት (ታኅሣሥ 29) ብቻ የሚከናወን አይደለም፤ እንዲያውም የዚያን ቀን በዓል ስለሆነ ላይጫወቱ ይችላሉ፡፡ የገና ጨዋታ የሚባለው ከታኅሣሥ ወር አጋማሽ ጀምሮ ያሉትን የበጋ ወራት በሙሉ ነው፡፡ ምንም እንኳን የገና ሰሞን የሚባለው ከታኅሣሥ ወር አጋማሽ በኋላ እስከ ጥር ወር መጀመሪያ ያለው ቢሆንም የገና ጨዋታው ግን እስከ የካቲት ወር ድረስ ይቀጥላል፡፡

‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም›› ጌታ የተባለው ከሌላው ወቅት በተለየ በዚህ ወቅት በነፃነት ስለሚጫወቱ ነው። በሌሎች ወራት (ለምሳሌ በክረምት እና በመኸር) በነፃነት ሊጫወቱ አይችሉም፡፡ ከብቶች (ፍየሎች) ወደ እህል ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ ቀልባቸው ተንጠልጥሎ አጫጭር ጨዋታዎችን ብቻ ነው የሚጫወቱት፡፡ ቤተሰቦቻቸው ወይም የእህሉ ባለቤት ይቆጧቸዋል፡፡ በገና ወቅት ግን ከብቶች ወዴትም ቢሄዱ የሚያጠፉት ነገር ስለሌለ የሚቆጣ ጌታ አይኖርም፡፡ ከገና በፊት ባሉት ወራት ግን በነፃነት አይጫወቱም፡፡ ለዚህም እንዲህ የሚል ጨዋታ አላቸው፡፡

**ከዱሩ ውስጥ ሆኜ መሰንቆ ስመታ**
**ፍየሎቼ ከሰው እህል ገብተው እኔሳ ብመታ!**

ጨዋታ ጨዋታዬን ሳይ ፍየሎቼ አምልጠውኝ ከሰው እህል ቢገቡ፣ የእህሉ ባለቤት ይገርፈኛል ማለቱ ነው፡፡

‹‹በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ›› ይባላል፡፡ ይህ ደግሞ ጨዋታው እየተለመደ እና ባሕል እየሆነ ስለሄደ ትልቅ ቦታ የተሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡ ጌታ እና ሎሌ ሳይኖር ሁሉም እኩል ይጫወታል ማለት ነው፡፡ ወይም ይህን ጨዋታ በመጫወቱ ቤተሰቦቹ የሚቆጡት ልጅ አይኖርም ማለት ነው፡፡ በጨዋታው ላይ ብዙ ባሕላዊ ድርጊቶች አሉ፡፡ ጉዳት የሚያደርስ ነገር እንኳን ቢከሰት በገና ጨዋታ ምክንያት ፀብ እንደማይፈጠር በተደጋጋሚ ይነገራል፡፡ ይህን ለባሕል ይዘት እንተወው፡፡

እንዲህ አይነት የገና ጨዋታ ባሕላዊ ይዘቶች እያሉን ነው እንግዲህ ስለፈረንጆቹ ‹‹ሳንታ ክላውስ›› ብዙ ትንታኔ እና ማብራሪያ የሚሰጠው፡፡ የገና ጨዋታን በተመለከተ ወደ በይነ መረቡ ዓለም ብትገቡ በጣም ተደጋጋሚ የሆኑ አንድ አይነት ማብራሪያዎችን ነው የምታገኙት፡፡ ሥነ ቃሎቹም አንድ አይነት ናቸው። እንደምንም ብሎ አንድ ሰው ኢንተርኔት ላይ ከጫነው ሬዲዮውም፣ ቴሌቪዥኑም ያንኑ ነው የሚያብራሩት። እርግጥ ነው በሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የተሻለ ነገር አለ፡፡ ቢያንስ በበዓሉ ዕለት የባሕል ባለሙያ ወይም የሃይማኖት አባት ተጋብዞ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

በዚህ ላይ የተሠሩ ጥናቶችን እንፈልግ ቢባል ግን እዚህ ግባ የሚባል አይኖርም፡፡ የተሠራ ካለም ምናልባትም ለመመረቂያ እንጂ ባሕሉን ለማስተዋወቅ ሲባል በምርምር ተቋም የተሠራ ማግኘት አይቻልም። ይህን የምለው ለገና ጨዋታ ብቻ አይደለም፡፡ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ባሕልና ትውፊት፣ የማኅበረሰብ ፍልስፍና የሆኑ ነገሮች ላይ በሀገርኛ ቋንቋ እና በሀገርኛ አቀራረብ ማግኘት አይቻልም፡፡ ብዙ ጥናቶች በውጭ ቋንቋ የሚሠሩ ናቸው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በጣም ግልጽ ነው፡፡ በቀላሉ ከኢንተርኔት መገልበጥ ስለሚቻል ነው፡፡ ከዚህኛው ጉዳይ ጋር ባይገናኝም ሰሞኑን ያጋጠመኝ አንድ ጥናት ልጥቀስ፡፡

ስለጥላሁን ግዛው የተሠሩ ጥናቶች ካሉ በሚል የበይነ መረቡን ዓለም ማሰስ ጀመርኩ፡፡ አንድ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፈ ‹‹ፒ ዲ ኤፍ›› ጽሑፍ አገኘሁ። ጽሑፉ በወቅቱ በነበሩ በአማርኛ ቋንቋ የተነገሩ የተማሪዎች መፈክሮች እና ግጥሞች የታጨቀ ነው፡፡ ቃላቱ የአማርኛ ናቸው፡፡ እነዚያን ሁሉ የመፈክር ቃላት እና ግጥሞች ግን በእንግሊዘኛ ፊደል ነው የጻፋቸው፤ ምክንያቱም ጽሑፉ በእንግሊዘኛ ስለሆነ፡፡

ጥናቱ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ከሆነ፣ የሚቀርበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሆነ፣ የቃል ግጥሞቹ ወደ እንግሊዘኛ ካልተተረጎሙ በእንግሊዘኛ መጻፉ ለምን አስፈለገ? እንዲያውም አንባቢን ጭምር ግራ ማጋባት ነው፡፡ የአማርኛ ግጥም በእንግሊዘኛ ፊደል ተጽፎ ምንም ስሜት አይሰጥም፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የምናየውም ይሄው ነው፡፡ ‹‹የባሕል ጥናት ጉባኤ›› ተብሎ ጥናቶች የሚቀርቡት በፈረንጅ ቋንቋ ነው፡፡ አዳራሹ ውስጥ ግን አንድም ነጭ የለም፡፡ በዚህ ምክንያት ሥነ ቃሎችን በትክክል አያስቀምጧቸውም፡፡ ከኢንተርኔት ማግኘት የሚቻለውን ብቻ ሰብስበው ያቀርባሉ፡፡ ያ ጥናት በየመገናኛ ብዙኃኑ ይሰራጫል ማለት ነው፡፡ ይህን የምለው ለአጠቃላይ ባሕሎቻችን እንጂ የገና ጨዋታን በተመለከተ ብቻ አይደለም፡፡

ወደ ገና ጨዋታ ስንመለስ፤ የገና ጨዋታ በተለይም ለእረኞች በጉጉት የሚጠበቅ በዓል ነው፡፡ ሰፊ ነፃነት ስላለው በዓልነቱም የተሻለ ይሆናል፡፡ ከዚያ ውጭ ባሉት በዓላት ሰፋ ያለ ጊዜ አይኖራቸውም፡፡ ገናን በጉጉት ከመጠበቃቸው የተነሳ በክረምት ወራት እንዲህ እያሉ ይጫወታሉ፡፡

**ፍየሌን ነብር በላት**
**ስገና ብየ ሳደሳድሳት!**

እንዲህ አይነት ሀገራዊ ትውፊቶች ስላሉን ከፈረንጆቹ ገና ይልቅ የራሳችንን የገና ባሕሎች እንወቅ!

# ዓለም አቀፍ



## የኖቤል ተሸላሚው እንዲታሰሩ የባንግላዴሽ ፍርድ ቤት ወሰነ

የባንግላዴሽ ፍርድ ቤት የኖቤል ተሸላሚው ፕሮፌሰሩ ሙሐማድ ዩኑስ ለስድስት ወራት እንዲታሠሩ አዘዘ። ፍርዱ የተላለፈው ሙሐማድ የሀገሪቱን የሠራተኛ ሕግ ተላልፈዋል በሚል ነው። ታዋቂው የምጣኔ ሀብት ባለሙያና እሳቸው በመሠረቱት ፕሮፌሰሩ ግራምን ቴሌኮም ተቋም የሚሠሩ ሦስት የሥራ ባልደረቦቻቸው ለተቋሙ ሠራተኞች ልዩ የክፍያ ሥርዓት በማዘጋጀት ጥፋተኛ ተብለዋል።

ሠራተኞቹ የተለያየ እክል ሲገጥማቸው የሚገለገሉበት ገንዘብ የሚሰጥበት ሥርዓት (ዌልፌር ፈንድ) ነበር ያቋቋሙት። አራቱም ተከሳሾች ስህተት አልሠራንም ሲሉ ተከራክረዋል። በጊዜያዊነት በዋስ እንዲወጡ ፈቃድ ተሰጥቷል። የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተከትሎ በሰጡት መግለጫ ፕሮፌሰሩ ሙሐማድ “ጠበቆቼ በአሳማኝ ሁኔታ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት መከራከሪያ መሠረት ፍርዱ ከምክንያታዊነት የራቀ ነው” ብለዋል።

“የባንግላዴሽ ሕዝብ ኢ-ፍትሐዊነትን በአንድ ድምፅ እንዲያወግዝና ለሁሉም ዜጎች ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት እንዲቆም እጠይቃለሁ” ሲሉም አክለዋል። የ83 ዓመቱ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ በመላው ዓለም የሚታወቁት ‘የድሆች መጠለያ’ በሚል ስም ነው። በማይክሮ ፋይናንስ ቀዳሚ ሥርዓት በመገንባትና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ከድህነት በማውጣት ይታወቃሉ።

ፕሮፌሰሩ እንዲሁም የመሠረቱት ግራመን ባንክ እአአ በ2006 ኖቤል ተሸልመዋል። ከጠበቆቻቸው አንዱ አብዱላህ አል ማሙን “ያልተጠበቀ ውሳኔ ነው። ሕግን ያልተከተለና የተጣደፈ ነው” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። “ሐሳቡ ዓለም አቀፍ ምስላቸውን ማጠልሸት ነው። ይግባኝ እንላለን” ሲሉም አክለዋል።

ከሠራተኞች ሕግ ጋር ይጻረራሉ በሚል ሌሎች 100 ክሶችም አሉባቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ሐሲና ሼክ የፕሮፌሰሩን ባንክ በአንድ ወቅት ‘ደም መጣጭ’ ሲሉ ገልጸውታል። ወለድ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመርም ከሰዋል። የቀድሞ የአምነስቲ የመብቶች ክፍል ኃላፊና አሁን በልዩ ልዑክነት በተባበሩት መንግሥታት የሚሠሩት አይሪን ካን፣ ለኤኤፒ እንዳሉት የፍርድ ቤቱ ውሳኔ “የፍትሕ መዛባት” ነው።

ባለፈው ነሐሴ 170 ዓለም አቀፍ የታዋቂ ሰዎች ስብስብ የባንግላዴሽ ጠቅላይ ሚኒስትር ፕሮፌሰሩን ‘ማንገላታት’ እንዲያቆሙ ጠይቀው ደብዳቤ አስገብተዋል። የቀድሞው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን፣ የቨርጅን ግሩፕ መሥራች ሪቻርድ ብራንሰን፣ የዩቱ መሪ ድምፅዊ ቦኖና ሌሎችም ፈርመዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሯ ግን ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተሉ ጋብዘዋል።

ፕሮፌሰር ሙሐማድ፤ አዋሚ ሊግ ፓርቲን የሚቀናቀን የፖለቲካ ፓርቲ ሊያቋቁሙ ስለሚችሉ ከጠቅላይ ሚኒስትሯ ጋር መሻከር ተፈጥሯል የሚሉ ቢኖሩም በትክክል የተከሰተው ግልጽ አይደለም ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## የደቡብ ኮሪያ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ በስለት ተወጉ

የደቡብ ኮሪያው ተቃዋሚ መሪ በሀገሪቱ ደቡባዊ የወደብ ከተማ ቡሳን ጋዜጣዊ መግለጫ በሚሰጡበት ወቅት በስለት መወጋታቸውን ዮንሃፕ የተባለው የዜና ወኪል ዘግቧል። እአአ በ2022 በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በጠባብ ውጤት የተሸነፉት ሊ ጃይ-ማዩንግ ማከሰኞ ጠዋት አንገታቸው ላይ ተወግተዋል ተብሏል። ጥቃት አድራሹ ወዲያውኑ በቁጥጥር ስር ውሏል።

አንድ ሴንቲ ሜትር ያህል ጉዳት የደረሰባቸው ሊ ወደ ሆስፒታል ተወስደው ሕክምና ተከታትለዋል። ቁስሉ ለሕይወታቸው አስጊ አይደለም ሲል ፖሊስ ገልጿል። በ50ዎቹ ወይንም በ60ዎቹ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ግለሰብ ወደ ሊ የቀረበው አድናቂያቸው በመምሰል ፊርማቸውን በመጠየቅ መሆኑ ተገልጿል።

ጥቃቱ ሲደርስ የሚያሳዩት እና በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተለጠፉት ቪዲዮዎች ሊ ከጥቃቱ በኋላ መሬት ላይ ሲወድቁ ያሳያሉ። ብዙ ሰዎች አጥቂውን ተጨማሪ ጥቃት እንዳያደርስ ለመግታት ሲሞክሩ ታይተዋል። ከክስተቱ በኋላ የተነሱ ፎቶግራፎች ላይ ሊ መሬት ላይ ዓይናቸውን ጨፍነው ተኝተው ሲያሳይ አንድ ግለሰብ ደግሞ በመሐረብ ቁስላቸውን ሲሸፍን አሳይተዋል።

በሄሊኮፕተር ወደ ሆስፒታል እንደተወሰዱም ዮንሃፕ ጨምሮ ዘግቧል። የ59 ዓመቱ ሊ የኮሪያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መሪ ናቸው። በአሁኑ ወቅት የደቡብ ኮሪያ ሕግ አውጪ አባል ባይሆኑም ከወራት በኋላ በሚካሄደው ምርጫ እንደሚወዳደሩ ይጠበቃል። እአአ በ 2022 በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በ0.73 በመቶ የድምጽ ልዩነት በአሁኑ ፕሬዚዳንት ዮን ሱክ ዮል ተሸንፈዋል። ይህ ምርጫ በደቡብ ኮሪያ ታሪክ ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ፕሬዚዳንታዊ ውድድር አድርጎታል።

እአአ በ2027 በሚካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እንደሚወዳደሩም በሰፊው ይጠበቃል። ከምርጫው ወዲህ ከሴዑል በስተደቡብ በምትገኘው እና አንድ ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባት የሴኦንግናም ከተማ ከንቲባ በነበሩበት ወቅት የግል አልሚዎች ከንብረት ፕሮጀክት በሕገ ወጥ መንገድ እንዲጠቀሙ ፈቅደዋል በማለት አቃብያነ ሕጎች በሙስና እና በእምነት ማጉደል ክስ መስርተውባቸዋል። ሊ ክሶቹን ውድቅ ከማድረግ ባለፈ ፖለቲካዊ ነው ብለውታል።

ፍርድ ቤት በመስከረም ወር በተከሰሱበት ጉዳይ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ የቀረበለትን የዓቃቤ ሕግ ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል። ዓቃቤ ሕግ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ከሙስና ጋር በተያያዙ ሌሎች በርካታ ክሶች እየመረመራቸው ነው። ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ያስተላለፈው የፕሬዚዳንት ዮንን የውጭ እና የሀገር ውስጥ ፖሊሲዎችን በመቃወም የረሃብ አድማ ማድረግ ከጀመሩ ከሦስት ሳምንታት በኋላ ነው። በአድማው ምክንያት ሊ ሆስፒታል ገብተው ለመታከም ተገደዋል።

የደቡብ ኮሪያ ፖለቲከኞች በጦር መሣሪያ አካላዊ ጥቃት ሲደርስባቸው አሁኑ የመጀመሪያው አይደለም። እአአ 2022 ከ ሊ በፊት ፓርቲውን ሲመሩ የነበሩት ሶንግ ያንግ-ጊል ለ ሊ ምርጫ ዘመቻው ሲያከናውኑ በደረሰባቸው ጥቃት ጭንቅላቱ ላይ ጉዳት ደርሶባቸው እንደነበር የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

# ባለውለታዎቻችን

# የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለውለታ

ክብረአብ በላቸው

በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ላይ ለሃምሳ አምስት ዓመታት የሠሩት አቶ ኃይሉ ገብረማርያም፤ ሲቪል ኢቪዬሽንን ድሮ እና ዘንድሮን የምናይባቸው ታላቅ ሰው ናቸው፡፡ ሕይወታቸው መማሪያ፣ ማወቂያ እና ነገን መመልከቻም ይሆናል፡፡ አቶ ኃይሉ ገ/ማርያም ትውልዳቸው በቀድሞ አጠራሩ በትግራይ ክፍለ ሀገር ዓድዋ አውራጃ ማይምሻም ተብላ በምትጠራ ቦታ ነው፡፡ ይህችን ምድር በወረሃ ሚያዝያ አስራ ዘጠኝ መቶ ሃያ አምስት ዓመተ ምሕረት ላይ ተቀላቅለዋል፡፡

ከእናታቸው ወይዘሮ ለምለም እንግዳ እና ከአባታቸው መምህር ገ/ማርያም ንጉሴ የተወለዱት አቶ ኃይሉ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በንግሥተ ሳባ ትምህርት ቤት ተምረዋል። በርካታ ተማሪዎች ጥቂት መምህራን የነበሩበት ትምህርት ቤት የተማሩት የወቅቱ ታዳጊው ኃይሉ እንደ እናት ያሳደጓቸው ታላቅ እህታቸው ወይዘሮ አወጣሽ ገ/ማርያም ነበሩ፡፡ አሳዳጊ እህታቸው ነገን በማሳብ የተሻለ ትምህርት ይገኝበታል ወደሚባለው አዲስ አበባ ለመላክ ቢያስቡም ወዳጅ ዘመድ ሁሉ እንዴት ካንቺ ተለይቶ ይሔዳል? ቢላቸውም የወንድማቸው ታላቅ የመሆን የወደፊት ሕይወትን በማሰብ ኃይሉ አዲስ አበባ እንዲሄድ ወሰኑ፡፡

ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ሆነ፤ ታላቅ ኃላፊነት ከተጣለባቸው ብላታ ገብሩ ተ/ሃይማኖት ጋር ከረዥም ጉዞ በኋላ ደረሱ፡፡ ትምህርታቸውንም ጥሩ ከሚባለው የተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ለመከታተል ቢያስቡም ጉዞ ላይ በመዘግየታቸው ሳይሳካ ቀረ፡፡ በመሆኑም ትምህርታቸውን በዓድዋ ቀጠሉ። ከዓድዋ ተጉዘው ዕውቀትን ፍለጋ አዲስ አበባን የረገጡት አቶ ኃይሉ፤ የስውዲሽ የሚሽን ትምህርት ቤትን በአስራ ዘጠኝ መቶ አርባ አራተኛ ክፍልን ተቀላቀሉ፡፡ ያላቸውን የትምህርት መቀበል ፍጥነት የተመለከቱት መምህራን ወደ አምስተኛ ክፍል አሸጋገሯቸው፡፡ በወቅቱ የስድስተኛ ክፍል ጓደኞቻቸው ደግሞ ፈተና በሚፈተኑበት ጊዜ ይዘዋቸው በመሄድ ተቀላቅለው አብረው ፈተናውን ወሰዱ፡፡ ቀድሞውኑ የዕውቀት ቀንዲል ነበሩ እና ከሌሎቹ በመብለጥ ካልደረሱበት ክፍል ፈተናውን በቀዳሚነት አለፉ፡፡

ይህንን ፈተና ላለፉ የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና መዘጋጃ ጊዜ ሆነ፡፡ ፈተናው የተሰጠው የአሁኑ ኮተቤ ሜትሮፖሊታን የቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ፈተናው ከወሰዱ በኋላ ግን በክረምቱ መሄጃ ስላልነበራቸው ኮተቤ ሰባተኛ ክፍልን ዘለው ስምንተኛ ክፍልን መማር ጀመሩ፡፡ በዚህ የቀጠሉት አቶ ኃይሉ የትምህርት ደረጃቸውን አሳደጉ፡፡

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤትም ፈተናው ቢከብድም አልፈው የዕውቀት ፈለጋቸውን ቀጠሉ፡፡ አስራ አንደኛ ክፍልን እንዳለፉ የቴክኒካል አቪዬሽን ኮሌጅ በዩናይትድ ኔሽን ተቋቁሟል ተብሎ በፊዚክስ፣ በሂሳብ ጥሩ ያስመዘገቡ አስራ ሁለት ተማሪዎች ተመርጠው ሲወሰዱ እርሳቸው አንዱ ነበሩ፡፡

የአቶ ኃይሉ ገብረማርያም የአቪዬሽን ጉዞ በ1945 ተጀመረ፡፡ ለአቶ ኃይሉ ቴክኖሎጂ ትልቅ ፍላጎት ብርቱ ዝንባሌያቸው የሚታይበት መሆን የጀመረው ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ነበር፡፡ በጊዜው በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ በነበረው ትልቅ ሳጥን ላይ በመመራመር ተጀመረ። የዘመኑ ሬዲዮ ላይ የዕውቀት መስመራቸውን ለመክፈት በመሞከር፤ ምርምራቸው ባገኙት ኤሌክትሮ ማግኔቲክ የሚል አዲስ ቃል ላይ በማብሰልሰል ለቴክኖሎጂ ፍላጎት አድሮባቸው ኖሮ የሲቪል አቪዬሽን መቀላቀል የእርሳቸው ወርቃማው ጊዜ ሆነ፡፡ በወቅቱ ሰላሳ የኪስ ብርም ይሰጣቸው ነበር፡፡

አስራ ሁለተኛ ክፍልን እንደጨረሱ ረዳት መምህር በመሆን በአንድ መቶ ሃምሳ ብር በርካታ ዕውቀትን መቅሰም ጀመሩ፡፡ ጊዜው ለአቪዬሽን ትልቁን መንገዳቸው በሰፊው ያመላከተም ነበር። በዚህ ወቅት የሲቪል አቪዬሽን ትምህርትንም ተከታትለው ጨረሱ፡፡ ጉዞው ግን በዚህ አላበቃም ወደ እንግሊዝ ለተሻለ ትምህርት አመሩ። በ1946 በእንግሊዝ በተመቻላቸው የነፃ የትምህርት ዕድል ለመከታተል በዛው ቢደርሱም፤ የመጣው ለአንድ ዓመት ነው የሚል ሃሳብ ተነሳ፡፡ ይሄ ግራ ቢሆንም በኋላ ግን የተሰጣቸውን ፈተና በማለፍ ከኤምባሲውም ጋር ግንኙነት በማድረግ ከኢትዮጵያ መንግሥትም ጫምሮ



አቶ ኃይሉ ገ/ማርያም

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፈቃድም ጭምሮ ሁለት ነፃ የትምህርት እድል አገኙ።

በእንግሊዝ ቆይታቸው ታላቅ የኢትዮጵያዊነት ፍቅር፣ ኩራት እና ክብርም ይሰማቸው ነበር። የሚያገኙዋቸውም በኢትዮጵያዊነታቸው ያከብሯቸው ነበር፡፡ በ1950ም በዛው የተማሪዎች ህብረት ተመሠረተ፡፡ በዚህም ወቅት ከእንግሊዝ የተማሪዎች ህብረት መስራቾች ውስጥ አንዱ ነበሩ፡፡ የኮሚቴውም ፀሐፊ ሆነው አገልግለዋል። ጥሩ ግንኙነት፣ የታቀዱ ሥርዓታዊ ውይይቶች የተካሄዱበት እና ትምህርትም የቀሰሙበት ነበር፡፡ በወቅቱ ሀገርን በሚያበለፅጉ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ እና በማህበራዊ አስተሳሰብ ላይም ሰርተዋል፡፡

የምህንድስና ትምህርታቸውን ለአራት ዓመታት ተከታትለው ተመልሰዋል፡፡ በ1954 በሀገራችን የሲቪል የአቪዬሽን ልማታዊ ሥራ ውጤታማ ለማድረግ እንቅስቃሴ የተጀመረበት ወቅት ነበር። እርሳቸው የተመለሱበት ይህ ወቅት የበረራ አየር ማረፊያ የግንባታ ሥራ ተጠናቆ የርክክብ ሂደት ላይ ነበር፡፡ የድሬዳዋ፣ አስመራ እና የጅማ አየር ማረፊያዎች የግንባታ ሥራቸውም እየተጠናቀቀ ነበር፡፡ አቶ ኃይሉ በሲቪል አቪዬሽን አስተዳደር በቴክኒካል ክፍል የራዳር እና ናቪጌሽን ግንኙነት ኢንጂነር ሆነው ባገለገሉበት ዘመን፤ በእንግሊዝ የቀሰሙትን ዕውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥ ቀን ከሌት እንቅልፍ አልነበራቸውም፡፡

በመሥሪያ ቤቱ የመገናኛ እና ኮሙዩኒኬሽን ሥራው ቀድሞ የተሠራ ቢሆንም ጥቅም ላይ ብዙም ሳይውል የቆየ ነበር፡፡ ይህም በአቶ ኃይሉ እና ጓደኞቻቸው አማካይነት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ለአየር መንገድ ሥራ ዋናው የሚዳው ሁኔታ ነው የሚሉት አቶ ኃይሉ፤ የቦሌ አየር ማረፊያ ደግሞ በወቅቱ የነበረው ሁለት አውሮፕላን ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለት ብቻ ቢሆኑም በአሜሪካኖች የተሰራው ሜዳ ችግር መፈጠር ጀመረ እና ማሻሻያ ያስፈልገዋል ተባለ። ይህን እንዲቆጣጠሩ ኃላፊነት የተጣለባቸው ዕውቀትን ከብልሃት የታደሉት አቶ ኃይሉ ነበሩ፡፡

በ1960 አውሮፕላን ለማብረር አሁን ላይ በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ፈቃድ የሚሰጠው በወቅቱ ደግሞ ፈቃዱ የሚገኘው የግድ ኤደን ወይም የመን ከነበረው የእንግሊዝ ቀኝ ገዢ ፈቃድ በማግኘት ነበር፡፡ አቶ ኃይሉም በዚሁ ጉዳይ ኢትዮጵያ በራሷ የአየር ክልል ለምንድነው እራሷን የማታስተዳድረው የሚለውን ለማጥናት ወደ እስራኤል ተላኩ፡፡

ጉዳዩን ሲያጠኑ የመኖች ከእንግሊዝ ነፃ ሊወጡ መሆኑን፤ ይህም ከሆነ ደግሞ ኢትዮጵያ ፈቃዱን ለማግኘት ቁጥጥሩ በግብፅ ስር እንደሚሆን አወቁ። አቶ ኃይሉ እንዴት ይሻላል ሲሉም ባገኙት ምላሽ ፈቃዱ በራሷ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ኢትዮጵያ በራሷ የአየር ክልል እራሷን ማስተዳደር እንድትችል በሚያደርገው ሥራ ላይ ለአንድ ሳምንት ባደረጉት ተምረው ሪፖርት አድርገውም የድርሻቸውን ተወጡ። ይህ ሥራቸው የእርሳቸው ታታሪነት እንዲሁ አርቆ አሳቢነት ማሳያ አንዱ ነው።

በ1966ም የባህር ዳር እና አክሱም ኤርፖርትን ጨምሮ በርካቶችን ዲዛይን ሲደረጉ ቦታውን የመረጡትም እርሳቸው ነበሩ፡፡ አቶ ኃይሉ የሲቪል አቪዬሽን መሥሪያ ቤት የፕላኒንግ ኮሚሽን በነበሩበት ወቅት አንድ አዋጅ ወጣ፡፡ አዋጁ አስደንጋጭ ነበር፤ ከፕሬዚዳንቱ በሱዳን የአየር ክልል በኩል የኢትዮጵያ አውሮፕላኖች እንዳያልፉ፤ አየር መንገዱን እንዳይጠቀሙ የሚል አዋጅ ተሰማ። በርካታ በረራዎች በሱዳን በኩል ይደረጉ ስለነበር ሁሉም ተደናገጠ፡፡ በጊዜው የፕላኒንግ ኃላፊ የነበሩት አቶ ኃይሉ ከችግሩ ይልቅ መፍትሔን መሻት ላይ ትኩረታቸውን አደረጉ፡፡

በወቅቱ ያለው አማራጭ የኢትዮጵያ አንድ አካል በነበረችው አስመራ አድርጎ ወደ ሳዑዲ አረቢያ በኤር ስፔስ ተጠቅሞ ሰሜን አፍሪካዊት ወደሆነችው ግብፅ መዳረሻ ማድረግ ነበር፤ ይህንን ለማድረግ ደግሞ የሳዑዲ አረቢያ ፈቃደኝነት በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎችን መተዋወቅ እና መግባባት የሚቻላቸው አቶ ኃይሉ፤ በአንድ ስብሰባ ላይ በሳዑዲ አረቢያ የሲቪል አቪዬሽን ከሚሰራ አቻቸው ጋር ተዋውቀው ስለነበር፤ በወቅት ከእርሱ ጋር ያለውን ነገር ተወያይተው ወዲያው ጊዜያዊ ፈቃድ አገኙ፡፡ አቶ ኃይሉ ለማሳመን ማን ብሏቸው የሚባልላቸው ዓይነት ሰው ስለነበሩ ተሳካ፡፡

ጥያቄው ግን ለምን ሱዳን ይህንን አዋጅ ማወጅ ፈለገች የሚለው ነው፡፡ ከመንግሥት የመጣው ሃሳብ እናንተም በተመሳሳይ የሱዳንን የአየር ክልል በኢትዮጵያ ዝጉ የሚል ነበር፡፡ ይህ የሚሆነው አንዳች የሚያተርፈው ጥቅም ሲኖር ነው፤ ታዲያ ሱዳኖች ምን ለማትረፍ ነው? እኛስ ብንዘጋ ምን እንጠቀማለን? ብለው ቀድመው ማሰላሰልን ያዙ። በተጨማሪም ይህ በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የፈረሟቸውን ሁሉ ስምምነቶችም ገደል የሚከት ነበርና ዕውቀታቸውን ከሕጉ ጋር ማጠመር ያዙ፡፡

ሰላማዊ ውይይት፣ መደራደርና መስማማት ያስፈልጋል የሚል እምነት ስላደረባቸው፤ ሱዳን የአየር ክልሏን እንድትፈቅድ የሚያስማማ ጽሑፍን ማሰናዳት ጀመሩ፡፡ ይህም በተጀመረበት ወቅት የአየር መንገድ ኃላፊዎችን ጨምሮ አምስት ሰዎችን ጓድ መንግሥቱ ሀ/ማርያም በተገኙበት በደርግ ጽ/ቤት ሀገራዊ ታላቅ ውይይት ተካሔደ፡፡

በስብሰባው ላይ ለሰላማዊ ድርደሩ የተዘጋጀው ጽሑፍ ተነበበ፡፡ ይህንን ተከትሎ በርካታ ጥያቄዎች መነሳት ጀመሩ፡፡ ሱዳን የአየር ክልሏን መዝጋት ሉዓላዊ መብቷ ነው የሚሉ እና የመሳሰሉ ዓይነት ሃሳቦች ተስተጋቡ፤ ሆኖም በጊዜው ከአቪዬሽን ተወክለው የሄዱት የሕግ አማካሪ አቶ አበራ መኮንን የአቪዬሽንን ሕግ ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር ተገቢውን ምላሽ ሰጡ፡፡

አቶ ኃይሉም ቢሆን በደርግ ጽ/ቤት በተሰበሰቡበት ወቅት በዕውቀት የታገዘ ምላሻቸውን አጋሩ፡፡ ዕውነታውን ከተጨባጭ ዕውቀት ጋር እያስተሳሰሩ ተናገሩ፡፡ አቶ ኃይሉ የመንግሥቱ ኃይለማርያም ምላሽ ምን እንደነበር ሲናገሩ ‹‹የያዛችሁት በዕውቀት የታገዘ ትክክለኛ ውሳኔ ነው፤ ቀጥሉበት፡፡›› ተብለው እንደተደነቁባቸው ገለፁ። መታገስ መልካም ነውና ሱዳኖችም ከአንድ ወር ድርድር በኋላ ታላቅ ይቅርታን አቅርበው ስጦታም ሰጥተው ግንኙነቱን እንደገና ማደስ ተችሏል።

አቶ ኃይሉ ገ/ማርያም የአቪዬሽንን ሙያ ዘልቀው እንደ ማጥናት እና መመራመራቸው በሁለት ሀገራት መካከል የአየር በረራ ግንኙነት መኖርን ከበፊት ጀምሮ ያምኑበት ነበር፡፡ ሥራን በጀመሩበት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን በአንዳንድ ሀገራት በረራ ይደረግ ነበር፤ ሆኖም በ1966 መንግሥት ሲቀየር በረራ የሚደረግባቸውን ሀገራትም የግድ ማስተካከል ያስፈልግ ነበር፡፡

ለሀገር ያላቸው ፍቅር ከፍተኛ የሆነው አቶ ኃይሉ ሥራ ላይም በታታሪነታቸው ይታወቃሉ፡፡ ከ1966 በኋላም ለሀገራችን የተለያዩ ሀገራት የአየር ክልላቸውን ክፍት እንዲያደርጉ ጥረት አድርገዋል። በተለያዩ ሀገራትም የአየር በረራ እንዲጀመርም አድርገዋል፤ ከእነዚህም መካከል ጋና፣ ኬንያ፣ የመን፣ አቡዳቢ፣ ባህሬን እና ጣሊያን ይነሳሉ፡፡ የአቶ ኃይሉ ህልማቸው በዕውን የተሳካ በመሆኑ ጥረታቸውም ከግብ በመድረሱ ስማቸው በጉልህ ሰፈረ፡፡

በሲቪል አቪዬሽን የፕላኒንግ እና የፖሊሲ ኃላፊ በነበሩበት ወቅት ደግሞ አንድ ያሳኩት ሌላ ቁምነገር ነበር፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አቢጃን ለመብረር ብዙ ጊዜ ሞክሮ አልተሳካለትም ነበር። በተጨማሪም አየር መንገዱ ትርፋማ ባለመሆኑ የመዘጋት እጣ ፋንታ ከፊቱ ተደቅኖበትም ነበር፤ የነበሩት አውሮፕላኖችም ከማርጀታቸው የተነሳ መላ ዘይዱላቸው የተባለበትም ጊዜ ነበር፡፡ አየር መንገዱ በዚህ ውስጥ ቢሆንም ወደ አቢጃን መብረር አለበት የሚል ቁርጥ አቋም ነበረ፡፡ ነገሩ ደግሞ እንዲህ በቀላሉ የማይቻል ነበር፡፡ ይህ የማይቻለው እንዲቻል ታምኖባቸው ታላቅ ሀገራዊ ኃላፊነት የተሰጣቸው ደግሞ አቶ ኃይሉ ነበር።

በዚህ ድርድር ሀገራችንን ወክለው ተጨማሪ ሰዎች ለድርድሩ መምጣት ቢኖርባቸውም በአውሮፕላን እጦት ሳይገኙ ቀሩ፡፡ ስለዚህ ሙሉ ኃላፊነቱ በእርሳቸው ላይ ወደቀ፡፡ አፍሪካዊያን ለአፍሪካዊያን ብቻ መወያየታቸው መፍትሔን እንደሚያመጣ ማሳያ የሆነው ድርድር ቀናት ቢወስድም ተሳካ፡፡ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የአየር በረራ ፈቃድን አሰጡ፡፡ ይህ በሁሉም ውስጥ መደነቅን የጫረ ነበር፡፡

ይህ የአቶ ኃይሉ ጥረት ከሀገራችን አልፎ በዓለም አቀፍ ሰዎች በጉልህ እንዲጠራም አድርጎታል፡፡ ሁ ኢዝ ሁ ኢን አቪዬሽን የተሰኘ የመረጃ መጽሐፍ እ.ኤ.አ በ1973 ባወጣው እትሙ የእርሳቸውን ስም በደማቅ ብዕሩ አስፍሮታል፡፡ በሶስት መንግሥታት ሥር ሀገራቸውን በታማኝነትና በቅንነት ያገለገሉት የሀገር ባለውለታ አቶ ኃይሉ ገብረማርያም ከወይዘሮ አሰፋሽ ጋር ትዳር መስርተው ሶስት ልጆችን ማፍራት ችለዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ሀገር አቀፍ የማህበረሰብ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዛሬ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

የዓመቱ የመጀመሪያ ዙር ብሄራዊ የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዛሬ ይካሄዳል። በመላው የሀገሪቷ ክፍሎች በሚደረገው በዚህ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ላይም ሚሊዮኖች ይሳተፋሉ በሚል እንደሚጠበቅ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር አስታውቋል፡፡

በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ በአካል ብቃት እንቅስቃሴ ተሳታፊ በመሆን ጤንነቱን እንዲጠብቅ ለማድረግ ማህበረሰብ አቀፍ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ስፖርት ዘርፍ ትኩረቱን ካደረገባቸው ጉዳዮች መካከል ቀዳሚው ሊሆንም ችሏል፡፡ ከዚህ ቀደምም በመላው የሀገሪቷ ክፍሎች ማህበረሰብ አቀፍ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች በስፋት ሲከናወኑ የቆዩ ሲሆን፤ በተያዘው ዓመት የመጀመሪያ የሆነው መርሀ ግብር ዛሬ የሚከናወን ይሆናል፡፡

በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር አዘጋጅነት የሚደረገው ንቅናቄው ‹‹የአንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሚሊዮኖች እና ለአብሮነት›› የሚል መሪ ሃሳብን አንግቧል፡፡

መርሀ ግብሩ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ከጠዋት ጀምሮ ሁሉም በያለበት ስፍራ እንዲሁም በተመረጡ ስፍራዎች የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች በተገኙበት ለአንድ ሰዓት ያህል የአካል ብቃት እንቅስቃሴው የሚደረግ ይሆናል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ላይም 12 ሚሊዮን ያህል ህዝብ ተሳታፊ ይሆናል ተብሎም ይጠበቃል፡፡ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፤ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን አንድ ላይ አሰባስቦ በማሳተፍ ህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስሩን እንዲያጠናክርና አብሮነቱን እንዲያዳብር ያለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡



በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣

የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መርሀ ግብር ስፖርትን ባህሉ ያደረገ በአካል እና በአእምሮ የጎለበተ ማህበረሰብ ለመፍጠር ትልቅ አበርክቶ እንዳለውም ሚኒስትር ዴኤታው አክለዋል፡፡ በስፖርት ተሰጥኦ ያላቸውን እና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የኢትዮጵያን ስም ከፍ አድርገው ሊያስጠሩ የሚችሉ ስፖርተኞችን በማፍራት ረገድም ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል። በመሆኑም መንግሥት ይህንን በመረዳት የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በሁሉም አካባቢ ተደራሽ ለማድረግ ፖሊሲ ቀርጾ እየሰራ እንደሚገኝም አስታውቋል፡፡

ለዚህ መርሀ ግብር አስቀድሞ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ ስፖርት ለማህበራዊ ልማት ያለውን አስተዋጽኦም እንደሚያሳይ የጠቆሙት ደግሞ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ ናቸው፡፡ ስፖርት አብሮነትንና ወንድማማችነት ለማስፋት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ከፍተኛ ዝግጅት በማድረግ አስቀድሞ በመርሀ ግብሩ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠርም ተችሏል። ከክልሎች ጋርም በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን ከመግባባት ላይ በመድረስ በተለይ በትምህርት ቤቶች ላይ በማተኮር የሚካሄድ ይሆናል፡፡ በዚህም አዲስ አበባን ጨምሮ በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ለማሳተፍ ታቅዷል፡፡

ከዚህ ባለፈ በየክልሉ በተመረጡ ስፍራዎች ላይ እንቅስቃሴው ይካሄዳል፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም በዋናነት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ውስጥ አመራሮች በተገኙበት የሚከናወን ይሆናል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ ላይ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ሶዶ፣ ሲዳማ ክልል በሃዋሳ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ በሆሳዕና(አርብ ዕለት ደግሞ በወልቂጤ ከተማ) በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ ክልሎች ላይም ይኸው ንቅናቄ በስፋት እንደሚከወን ታውቋል፡፡ የማህበረሰብ አቀፍ አካል ብቃት እንቅስቃሴው በዓመቱ በአራት ዙር የሚካሄድ ሲሆን፤ በየካቲት፣ ሚያዝያ እንዲሁም ሰኔ ወሮች ላይ በመላው ሀገሪቷ ለማካሄድ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑንም አቶ ተስፋዬ ጠቁመዋል፡፡

በ2015ዓ.ም በተደረገው ብሄራዊ የማህበረሰብ አቀፍ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች አምስት ሚሊዮን ያህል ህብረተሰብን ለማሳተፍ ታቅዶ 5ነጥብ4 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎችን ተካፋይ ማድረግ ተችሏል፡፡ በቀጣይም የተሳታፊዎችን ቁጥር በመጨመር በዓመት አራት ጊዜ ለማካሄድ እንደታቀደና ሰፊ እንቅስቃሴ እንደተጀመረ ገልጸዋል፡፡

ከዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የዩኒቨርሲቲው የትኩረት አቅጣጫዎች

በስጥሻቸው ልዑልሰገድ

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በ2004 ዓ.ም የተመሰረተ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት የመማር ማስተማር ስራውን የማከናውን፣ የተለያዩ ምርምሮችን የመስራት እና ለአካባቢው ማህበረሰብ የማህበረሰብ አገልግሎት የመስጠጥ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፡፡ ይህንንም ተልዕኮ ለማሳካት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በዛሬው እትማችን ዩኒቨርሲተው የሚሰራባቸውን የትኩረት አቅጫዎች አስመልክቶ የዩኒቨርሲተው የህዝብ ግንኙነትና አለም አቀፍ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ገዴ ጋር ያደረግነውን ቆይታ ክፍል አንድ እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበናል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በ2004 ዓ.ም የመማር ማስተማር ስራውም የጀመረው በአራት ፋካልቲዎች 538 ተማሪዎችን በመቀበል ነው የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ ዛሬ ላይ ይህ ዩኒቨርሲቲ 68 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 78 የሁለተኛ ዲግሪ እና ሰባት የሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች ከፍቶ ተማሪዎችን በመቀበል ላይ ይገኛል፡፡ በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች ከ30 ሺህ በላይ ተማሪዎችን በሶስት ካምፓሶች በማስተማር ላይ የሚገኝ እና የመማር ማስተማር ስራውን የሚከናውንባቸው ስምንት የማስተማሪያ ማዕከላት ያሉት ዩኒቨርሲቲም ነው ይላሉ፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ይህ ዩኒቨርሲት በ2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከሚገኙ ምርጥ 10 ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ የመሆን ራዕይ ይዞ በመስራት ላይ ነው፡፡ ይህንን ራዕይ ለማሳካትም አራት የትኩረት አቅጣጫዎችን ቀርፆ ይንቀሳቀሳል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ የትኩረት አቅጣጫ አግሮ ፕሮሰሲግ (ግብርና) ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ዩኒቨርሲቲው በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ የወተት ላሞችን በማርባት በቀን እስከ 200 ሊትር ወተት ያመርታል፡፡ ወተቱን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ለከተማዋ ነዋሪዎች ገበያ ላይ ካለው ዋጋ በግማሽ ባነሰ ዋጋ እንዲዳረስ ይደርጋል፡፡

በተጨማሪም የዶሮ እርባታ እና የእንቁላል ምርት ላይ እየሰራ የሚገኘው ዩኒቨርሲቲው ያሉትን የዶሮ ጫጩቶች ቁጥር 10 ሺህ ለማድረስ እየሰራ ነው። የአፕል ምረትም ዩኒቨርሲቲው ትኩረት ሰጥቶ እየሰራባቸው ካሉ የግብርና ምርቶች መካከል አንዱ ሲሆን በስንዴ፣ በማር እንዲሁም በሌሎች የሰብል ምርቶች ላይ ምርታማ ለመሆን እየተጋ ይገኛል፡፡ ከአፕል ብቻም በአመት ሁለት ጊዜ እስከ ሶስት መቶ ኩንታል ምርት ይሰበሰባል፡፡

ይህ የግብርና ስራ መከናወኑ ዩኒቨርሲቲው የውስጥ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው ከማድረጉ ባሻገር ማህበረሰቡን እየፈተነ ያለውን የኑሮ ውድነት ከመቀነስ አንፃር የራሱን ሚና እንዲጫወት አድርጎታል የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ባሻገር በግብርናው ዘርፍ የተቀናጀ የግብርና ዘሮች የሚመረቱበት የተለያዩ ማሳዎችን በመፍጠር እንደድንች፣ ቀይስራ፣ እና አቮካዶ የመሳሰሉ ምርቶችን በማምረት መንግስት ያስቀመጠውን የትኩረት አቅጣጫ በመከተል የሌማት ትሩፋትን ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

አቶ ዳንኤል እንደሚናገሩት፤ ዩኒቨረሲቲው የአግሮ ፕሮሰሲግ (ግብርና) የትኩረት አቅጣጫን ለማሳካት ስምንት የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ እያንዳንዱ የምርምር ማዕከል የሚያተኩርበት የምርምር ጉዳይ ተለይቷል፡፡

በዚህም መሰረት ‘ኢሾ’ የቡና ምርምር አንዱ ማዕከል ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ የቡና ችግኞች ስርጭት በዚህ የምርምር ማዕከል አማካኝነት ተከናውኗል፡፡ ‘ሾንቆላ’ በመባል የሚታወቀው የምርምር ማዕከል ደግሞ ደንን የሚመለከቱ ምርምሮች የሚከናወኑበት ማዕከል ነው፡፡ በሃዲያ ከተማ ሶስት ሰንሰለታማ ተራሮች አሉ፡ ፡ በነዚህ ተራሮች ላይ የተለያዩ ለደን የሚሆኑ ተስማሚ የዛፍ ችግኞች በምርምር ለይቶ ችግኝ የማፍላት እና ለማህበረሰቡ የማሰራጨት ስራ ይከናወናል፡፡

ሌላኛው የምርምር ማዕከል ‘ለምቡዳ’ በመባል የሚጠራው ነው፡፡ በዚህ ማዕከል በዋናነት በአፕል እና በአቮካዶ ምርት ላይ ያተኮሩ የምርምር ስራውች ይሰራሉ፡፡ በ’አርጫ’ የምርምር ማዕከል ደግሞ በሙዝ ላይ ምርምር ማድረግ ጀምሯል፡፡ በቆሎና ጤፍ ላይም እንዲሁ ምረምሮች በመካሄድ ላይ ናቸው። በ’ዱራሜ’ የምርምር ማዕከም በዋናነት ሁሉንም ምርቶች የአካባቢውን አግሮ-ኢኮሎጂ በጠበቀ መልኩ የማምረት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

‘ቡማ’ በመባል በሚታወቀው የምርምር ማዕከልም እንዲሁ የእንሰት እና የአፕል ምርቶች ላይ ምርምሮች ይሰራሉ፡፡ ምርትም እንዲመረት ይደረጋል። በዩኒቨርሲቲው ዋና ጊቢ ሁሉንም ያጠቃለለ ምርምር የሚሰራ ሲሆን የአካባቢው ማህበረሰብ ከእንሰት ምርት ጋር ያለው ቁርኝት ከፍተኛ በመሆኑ በሽታን መቋቋም እና ብዙ ምርት መስጠት የሚችሉ የእንሰት ዝርያዎችን በመለየት ለገበሬው ለማዳረስ የሞዴል አርሶ አደር ልየታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጠው የትኩረት አቅጣጫ ሜዲካል ቱሪዝም ነው፡፡ በደርግ ዘመን በህዝብ ተሳትፎ የተገነባው የንግስት እሌኒ መታሰቢያ ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስታል በግቢው ውስጥ የነበረው አንድ ህንፃ ብቻ ነው፡፡ በአሰራር ሂደትም ሆነ በመሰረተ ልማት የማስፋፊያ ስራ ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ይሄንን አንዱ የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይህንን ሆስፒታል በባለቤትነት ከተቀበለ በኋላ በአንድ አመት ውስጥ ብቻ ሰባት ህንፃዎችን ለመገንባት ችሏል፡፡

በሜዲካል ቱሪዝም ዘርፍ ዩኒቨርሲቲው ያከናወነው ሌላኛው ተግባር የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ፕሮግራሞችን ቁጥር መጨመር ነው፡፡ በ2011 ዓ.ም በኮሌጁ የሚሰጡ ፕሮግራሞ ቁጥር ሰባት ብቻ የነበሩ ሲሆን አሁን ላይ ግን ከ70 በላይ የስፔሻሊቲ ፕሮግራሞች በኮሌጁ እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡ ወደፊትም የሆስፒታሉ መሰረተ ልማትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ አለም አቀፍ ሆስፒታል እንዲሆን የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው አቅራቢያ በሚገኝ ‘ኪልግሳ’ በመባል በሚታወቅ ቦታ ሶስት ትልልቅ ስራዎች በመሰራት ላይ እንደሆኑ የሚናገሩት ዳይሬክተሩ፤ አንደኛው የእናቶችና የህፃናት ማዕከል ለብቻው እየተሰራ በመሆኑ እናቶችና ህፃናት ለብቻ ህክምና የሚያገኙበትና በሀገር ደረጃ ሪፈር የሚደረግበት ራሱን የቻለ የህክምና ማዕከል እንደሚኖር ያስረዳሉ፡፡

በህክምናው ዘርፍ ዩኒቨርሲቲው የሚሰራው ሌላኛው ስራ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ፕሮጀክት ነው፡፡ ህንፃውም ብዙ የግንባታ ስራዎቹ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኦክስጂን ማምረቻም እንዲሁ ዩኒቨርሲቲው በትኩረት የሚሰራበት ሌላኛው መስክ ነው፡፡ ከሆሳዕና አዲስ አበባ 230 ኪ.ሜ አካባቢ በመሆኑ ወደ አዲስ አበባ በመሄድ መታከም ያለባቸው ታካሚዎች በኦክስጂን አጥረት መንገድ ላይ ህይወታቸው የማለፍ እድሉ ከፍተኛ በመሆኑ ይህንን ለመቀነስ ዩኒቨርሲቲው የኦክስጂን ማምረቻ ላይ በደንብ መስራት አለበት። ከ540 በላይ አልጋዎች የያዘ የኦክስጂን ማምረቻ በአንድ ወር ውስጥ አገልግሎት መስጠጥ ይጀምራል ተብሎ ይታመናል። ይህንን ተከትሎም የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ራሱ የቻለ አንድ ካማፓስ ይሆናል ሲሉ ያብራራሉ፡፡